አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፪
አዲስ አበባ ፳፻፪ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Second year No.2
ADDIS ABABA 2009

ማውጫ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዥ
እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ

*Content*

THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT PROCUREMENT AND PROPERTY ADMINSTRATION PROCLAMATION

## አዋጅ ቁጥር ፲፯/ ፳፻፪

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት የግዥ ሥርዓትን ለመወሰን የወጣው አዋጅ በሥራ ላይ በቆየባቸው ዓመታት የታዩ የግዥ አፈጻፀም ችግሮችን በማስወገድ የመንግስት የግዥ ሥርዓት ይበልጥ ግልፅ፣ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና አድሎ የሌለበት እንዲሁም ለግዥ የሚውለውን ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ቁጠባንና ዉጤታማነትን ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ጥቅም ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከፍተኛ ሀብት የሚፈስበት የመንግሥት ንብረት ለከተማ አስተዳደሩ የተሻለ ጥቅም በሚያስገኝ አኳኋን ጥቅም ላይ እንዲውል እና አስተዳደሩም ዘመናዊ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል የተቀናጀ ሥርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባ የታመነበት በመሆኑ፤

## Proclamation No. 17/2009

## THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT PROCUREMENT AND PROPERTY ADMINSTRATION PROCLAMATION

**WHEREAS,** it is found necessary to achieve better transparency, efficiency, fairness and impartiality in public procurement and to enable the utilization of the large sum of public money spent on procurement in a manner that ensures saving and efficiency by addressing problems encountered in the course of implementation of the Proclamation determining the procedures of public procurement of the Addis Ababa City Government ;

**WHEREAS,** it is believed to ensure that public property in which a significant amount of public money is invested, is utilized in such a manner as to enable the government devise maximum benefit there from and modernize the administration thereof, it is necessary to introduce an integrated public property administration;

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

ያንዱ ዋጋ 21.35
Unit Price

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ ዓ.ም አንቀፅ ፲፬ (፩) (ረ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## ጠ ቅ ላ ላ

፩ አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፲፯/ ፪ሺ፪» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪ ት ር ጓ ሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩. «ዕቃ» ማለት በጠጣር፣ በፈሣሽ ወይም በጋዝ መልክ የሚገኝ ጥሬ ዕቃ፣ ምርት፣ መሣሪያ፣ ሸቀጥ ፣ ለገበያ የተዘጋጀ ሶፍት ዌር፣ እንስሳ ሲሆን ከሚገዛው ዕቃ ጋር ግንኙነት ያለውን እና ከዕቃዎቹ ዋጋ ያልበለጠ ዋጋ ያለው የተከላ፣ የትራንስፖርት የጥገና እና ሌላ ተመሳሳይ አገልግሎት ይጨምራል፡፡

፪. «አገልግሎት» ማለት ከዕቃ፣ ከግንባታ ዘርፍ ሥራ እና ከምክር አገልግሎት ውጪ ያለ ሲሆን፣ የጥገና፣ የጥበቃ ፣ የፅዳት አገልግሎት ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን እና የውሃ አቅርቦት የመሳሰሉትን ይጨምራል፡፡

፫. «የግንባታ ዘርፍ ሥራ» ማለት ከሕንፃ፣ ከመንገድ ወይም ከመሠረተ-ልማት ሥራ ጋር በተያያዘ የሚከናወን አዲስ የግንባታ፣ የመልሶ ግንባታ፣ደረጃ የማሳደግ፣ የማፍረስ፣ የጥገና፣ የማደስ ሥራ እንዲሁም ተጓዳኝ የሆነና ከዋናው ሥራ ያልበለጠ ዋጋ ያለው አገልግሎት ሲሆን፣ የመገንባት፣ በባለቤትነት የመያዝ፣ ሥራውን የማንቀሳቀስ፣ የማስተላለፍ፣ ውሎችን ይጨምራል፡፡

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 14(1) (f) of the Revised Charter of Addis Ababa City Government Proclamation No.361/2003 it is hereby proclaimed as follows;

## CHAPTER ONE

## GENERAL

***1. Short Title***

This Proclamation may be cited as «The Addis AbabaCity Government Procurement and Property Administration Proclamation No. 17/2009».

***2. Definitions***

In this Proclamation unless the context requires other wise:-

1. «Goods» means raw material, products and equipment and commodities in solid, liquid or gaseous form, marketable soft ware and live animals as well as installation, transport, maintenance or similar obligations related to the supply of the goods if their value does not exceed that of the goods themselves;
2. «Service» means any object of procurement other than works, goods and consultancy services such as maintenance, security, janitorial, electricity, telecommunication and water supply services;
3. «Construction Sector Works» means all works associated with the construction, reconstruction, up grading, demotion, repair or renovation of a building road, or infrastructure, which is a service related to and has value not exceeding that of the main work itself and includes contracts of building, holding in ownership, operating the work, or transferring.

፬. «የምክር አገልግሎት» ማለት አማካሪዎች ያላቸውን ሙያዊ ክህሎት በመጠቀም የሚሰጡት የጥናት፣ የዲዛይን እና ቁጥጥር፣ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን የማደራጀት፣ ለደንበኞች ምክር የመስጠት፣ ሥልጠና የመስጠት እና ዕውቀትን የማስተላለፍ የአማካሪነት ባህሪ ያለው የአዕምሮ አገልግሎት ነው፡፡

፭. «ግዥ» ማለት ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን እና አገልግሎቶችን በግዥ፣ በኪራይ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ውል ማግኘት ነው፡፡

፮. «አስተዳደር» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

፯. «የመንግሥት መሥሪያ ቤት» ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በከተማ አስተዳደሩ በጀት የሚተዳደር የመንግሥት መ/ቤት፣ የትምህርት ተቋም እና ተመሳሳይ አቋም ያለው አካል ነው፡፡

፰. «የመንግሥት ገንዘብ» ማለት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግምጃ ቤት ወይም የውጭ ዕርዳታና ብድር ለመንግሥት መሥሪያ ቤት የተመደበ ገንዘብ ወይም የመ/ቤቱ የውስጥ ገቢ ነው፡፡

፱. «የመንግሥት ግዥ» ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት በመንግሥት ገንዘብ የሚከናወን ግዥ ነው፡፡

፲. «አቅራቢ» ማለት ለመንግሥት መሥሪያ ቤት ዕቃ ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራ ለማከናወን ውል የገባ ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡

፲፩. «ዕጩ ተወዳዳሪ» ማለት በመንግሥት ግዥ እንዲሳተፍ የተጋበዘ ወይም ለመካፈል ያመለከተ ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡

፲፪. «ተጫራች» ማለት የመጫረቻ ሀሳብ ያቀረበ ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡

4. «Consultancy Service» means a service of an intellectual and advisory nature provided by consultants using their professional skills to study, design and organize specific projects, advise clients, conduct training and transfer knowledge;

5. «Procurement» means obtaining goods, works, consultancy or other services through purchasing, hiring or obtaining by any other contractual means;

6. «Government» means the Addis Ababa City Government;

7. « Public Body» means any public body, which is partially or wholly financed by the City Government budget; higher education institu tions and public institutions of like nature;

8. «Public fund» means any monetary source appropriated to a public body from the City government treasury or aid grants and credits put at the disposal of the public bodies by foreign donors through the Government or internal revenue of the public body;

9. «Public Procurement» means procurement by a public body using public funds;

10. «Supplier» means a natural or juridical person under contract with a public body to supply goods, works or services;

11. «Candidate» means a natural or juridical person invited to take part in public procurement or seeking to be so invited;

12. «Bidder» means a natural or juridical person submitting a bid;

፲፫ «የጨረታ ሰነድ» ማለት ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት እንዲችሉ በመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚዘጋጅ ዝርዝር የግዥ ፍላጎትን የሚገልፅ ሰነድ ነው::

፲፬ «የመጫረቻ ሰነድ» ማለት የመንግስት መ/ቤት ለግዥው ባዘጋጀው የጨረታ ሰነድ መነሻነት ተጫራች በግዥው ለመሳተፍ የሚያቀርበው ሰነድ ነው::

፲፭ «የግዥ መመሪያ» ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚወጣ መመሪያ ነው::

፲፮ «ሰው» ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

፲፯ «የቢሮ ኃላፊ እና ቢሮ» ማለት እንደቅደም ተከተሉ የፋይናንስና የኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ እና የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ነው::

፲፰ «ልዩ ግዥ» ማለት በከተማ ደረጃ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆኑ ምክንያት በቢሮ ውሣኔ በጥቅል የሚፈፀሙ ከፍተኛ ግዥዎች ወይም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ያላቸውን ተመሳሳይ የግዥ ፍላጎት እንዲሁም አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚኖረውን የግዥ ፍላጎት ለማሟላት የሚፈፀም ግዥ ነው::

፲፱ «የማዕቀፍ ስምምነት» ማለት ወደፊት በሚፈፀም ዝርዝር ውል ለሚከናወን አቅርቦት መሠረት በመሆን የሚያገለግል፣ በነጠላ ዋጋ እና በሌሎች የውል ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የተፈፀመ አጠቃላይ የሆነ የግዥ ስምምነት ነው::

፳ «የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢ» ማለት በማዕቀፍ ስምምነት ዕቃ ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ለማቅረብ ውል የገባ አቅራቢ ነው::

13. «Bidding Documents» means a document prepared by the public body as a basis for preparation of bids; which contains a specification of the desired object of procurement;

14. «Bid Proposal» means a document submitted by bidders to participate in a bid on the basis of the bid document prepared by a public body in respect of that procurement;

15. «Procurement Directive» means the directive to be issued by the Finance and Economic Development Bureau in accordance with this Proclamation;

16. «Person» means a physical person or an entity entrusted with personality by law.

17. «Head of Bureau and Bureau» means the Head of Finance and Economic Development Bureau and Finance and Economic Development Bureau respectively;

18. «Special procurement» means a procurement of sizable volume carried out in bulk by a decision of the head of the Bureau on account of the city level significance of that procurement or to fulfill similar requirements of various public bodies or requirements of a public body within a given period of time;

19. «Framework Contract» means a general agreement of procurement establishing unit price and other terms and conditions of contract which serves as a basis for supplies to be derived under future specific contract;

20. «Framework Contract Supplier» means a supplier who has entered in to a contractual obligation to supply goods or services under a framework contract;

፳፩. «የመንግስት ንብረት» ማለት ከመንግስት ገንዘብ እና መሬት በስተቀር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሐብት የሆነ ማናቸውም ንብረት ነው::

፳፪. «የጥበቃ ኃላፊነት» ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም ኃላፊው በወከለው የሥራ መሪ፣ የመንግሥት ንብረት እስከሚወገድ ወይም ከመዝገብ እስከሚሠረዝ ወይም በሌላ ሠራተኛ ወይም መ/ቤት ጥበቃ ሥር እንዲውል እስከሚተላለፍ ድረስ የመንግሥት ንብረት ለመያዝና ለመጠበቅ፣ ለመንግሥት ሠራተኛ የሚሰጥ ኃላፊነት ነው::

፳፫. «ቋሚ ንብረት» ማለት ግዙፋዊ ሀልዎት ያለው፣ የተናጠል ዋጋው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን፣ ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ የጠቀሜታ እሴት የሚኖረው እና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ንብረት ሲሆን፣ እንደ የቢሮ ዕቃ፣ ኮምፒውተር፣ ከባድመሣሪያ፣ ተሽከርካሪ፣ መርከብ፣ አውሮፕላን፣ ሕንጻ፣መንገድ፣ የፍሳሽ መስመር፣ ድልድይ፣ መስኖ እና ግድብ የመሳሰሉትን ይጨምራል::

፳፬. «የሕይወት ዘመን ሥርዓት» ማለት ከመንግሥት ንብረት ጋር የተያያዙ ተግባሮች እና ወጪዎችን የማቀድ፣የመያዝ፣የመረከብ፣ የመጠቀም፣ የጥገና፣ የፍጆታ ወይም የማስወገድ ወይም ከመዝገብ የመሠረዝ ተግባራትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የመንግሥት ንብረት አስተዳደር እና ቁጥጥር ብቃት ባለው መንገድ እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ነው::

፳፭. «አላቂ ዕቃ» ማለት ከቋሚ ዕቃ ውጪ የሆነ ማናቸውም የመንግሥት ንብረት ሲሆን፣ ጥቅም ላይ መዋል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል እና ዋጋው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ንብረት ነው::

21. «Public Property» means any property of the City Government other than public fund and land;

22. «Custodial Relationship» means the responsibility conferred on a civil servant by the head of a public body or by a person delegated by him to protect and maintain public property until its disposal or written off, or transfered to the custody of another civil servant or public body;

23. «Fixed Asset» means tangible asset the value of which is determined by a directive to be issued by the Bureau, that is in operational use and that has a useful economic life of more than one year, such as furniture, computer, heavy equipment, vehicles, ships and air craft, buildings, roads, sewers, bridges, irrigation systems, dam and the like;

24. «Life Time Approach» means a system of effective management and control of public property which takes in to account all associated activities and costs, namely planning, acquisition, receipt, use, maintenance, consumption or disposal of selection of public property;

25. «Supplies» means all public property other than fixed assets, which can be consumed within one year of use and the value of which is determined by a directive to be issued by the Bureau.

፳፮ «ማስወገድ» ማለት የመንግሥትን ንብረት በሽያጭ ወይም በዝውውር ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ወይም መቅበር ወይም ማቃጠል ነው።

፳፯ «የመንግሥትና የግል ሽርክና» ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት እና በግል ባለሀብት መካከል በሚደረግ ውል በግሉ ባለሀብት ተሳትፎ የሚደረግ ኢንቨስትመንት ሲሆን ኮንሴሽነር ተብሎ የሚታወቀው የግል ባለሀብት፣

ሀ) የግንባታ ፕሮጀክቶችን ወይም አገልግሎቶችን ወይም በኮንሴሽን ኪራይ የሚሰጡ ሥራዎችን ለማከናወን ግዴታ የሚገባበት፣

ለ) የመንግሥት ተግባር የሆኑ ሥራዎችን ከማከናወን ወይም የመንግሥትን ንብረት ሥራ ላይ ከማዋል ጋር በተያያዘ በፋይናንስ፣ በቴክኒክ እና በሥራ እንቅስቃሴ ረገድ የሚኖሩ ኃላፊነቶችን በአመዛኙ የሚወሰድበት፣

ሐ) የመንግሥት ተግባር የሆኑ ሥራዎችን በማከናወን ወይም የመንግሥትን ንብረት ሥራ ላይ በማዋል ለሚሰጠው አገልግሎት ከመንግሥት ክፍያ የሚያገኝበት ወይም በተጠቃሚዎች ላይ ከሚጣል ክፍያ ገቢ የሚሰበስብበት ወይም በሁለቱም መንገዶች ለአገልግሎቱ ክፍያ የሚያገኝበት፣ ውል ነው።

፳፰ «ኮንሴሽነር» ማለት ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር የመንግሥትና የግል ሽርክና ውል የሚገባ ሰው ነው።

26. «Disposal» means the transfer of public property to another person by sale or other means or the act of getting rid of public property by burning or burying;

27. «public-private Partnership »means investment through private sector participation by a contractual arrangement between a public body and a private sector enterprise, as the concessionaire, in which the concessionaire:

a) Undertakes to perform or undertake any construction project or service or lease concession;

b) Assumes substantial financial, technical and operational risks in connection with the performance of a public function or use of government property; and

c) Receives consideration for performing a public function or utilizing government property, by way of fees from any public funds, user levies collected by the concessionaire from users or customers for a service provided by it, or a combination of such consideration;

28. «Concessionaire » means a person who enters into a contract with a public body under a public-private partnership;

<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

፩ ይህ አዋጅ በማናቸውም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ቢኖርም፣

ሀ) የአስተዳደሩ ካቢኔ አግባብ ካላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ጋር በመመካከር በከተማው ደህንነት ምክንያት ግዥ እና የንብረት አስተዳደር በከተማው ደህንነት ዘዴ እንዲፈፀም ውሣኔ ሊሰጥ ይችላል:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ የቢሮ ኃላፊ ግዥ እና የንብረት አስተዳደር በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም ለማድረግ የሚያስችል የተለየ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ዘዴ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል መመሪያ ያወጣል::

ለ) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን፣ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶችን ወጪ በመሸፈን ከሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለማግኘት በሚያደርጉት ውል ላይ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

፬ የፆታ አገላለጽ

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ እስካልሆነ ድረስ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል::

፭ <u>የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር መርሆዎች</u>

የመንግስት ግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አስተዳደር የሚከተሉትን መርሆዎች መሠረት ማድረግ ይኖርበታል:-

፩ በግዥ አፈፃፀም ረገድ የመንግሥት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘቱ፣

፪ በዚህ አዋጅ በተፈቀደው ልዩ አስተያየት ካልሆነ በስተቀር በዜግነት ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል አድልዎ ያለመደረጉን፣

፫ ማናቸውም የግዥ ውሣኔ የሚሰጥበት መስፈርት እና በእያንዳንዱ ግዥ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልፅ እና ፍትሐዊ መሆኑን፣

### 3. *Scope of Application*

1. This proclamation shall apply to all Addis Ababa City Government procurement and property administration.
2. Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article:
   a) The Cabinet of the City Government, in consultation with the heads of the relevant public bodies, may decide to use a different procedure of procurement and property administration in which case the Head of Bureau shall define by a directive the method of procurement and property administration to be followed in order to serve the interest of economy and efficiency:
   b) This proclamation does not apply to contracts a public body enters into with another public body for the provision of goods, works, consultancy or other services at cost:

### 4. *Gender Reference*

In this proclamation, unless the context demands otherwise, expressions in the masculine gender also refer to the feminine gender.

### 5. *Principles of Public Procurement and Property Administration*

Public procurement and property administration shall have to comply with the following principles:-

1. ensure value for money in the use of public fund for procurement;
2. non-discrimination among candidates on grounds of nationality or any other criteria not having to do with their qualification, except in cases of preference specifically provided for in this Proclamation;
3. transparency and fairness of the criteria on the basis of which decisions are given in public procurement as well as of decisions in each procurement;

፬ ውሣኔዎች እና የተወሰዱ እርምጃዎች ተጠያቂነት የሚያስከትሉ መሆኑን፣

፭ የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ መያዝና ለታለመለት አላማ መዋሉን፣

## ፮. ዓለም ዓቀፍ ግዴታዎች

፩. ይህ አዋጅ አስተዳደሩ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ መንግሥታት ወይም ከዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ወይም በሚያደርገው ስምምነት ወይም ከስምምነቱ ከመነጨ ግዴታ ጋር የማይጣጣም ከሆነ በስምምነቱ የተመለከተው ይፀናል፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ስምምነት ለኢትዮጵያ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆኑ ተጫራቾች ልዩ አስተያየት የሚፈቅድ በሚሆንበት ጊዜ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ተፈፃሚ የሚሆነውን ልዩ አስተያየት በጨረታ ሰነድ ውስጥ በግልፅ ማመልከት አለበት፡፡

## ፯ የግዥ ሰነዶችን ሕዝቡ እንዲያውቅ ስለማድረግ

ይህ አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በቢሮው የሚወጡ የግዥ እና የንብረት መመሪያች እና ሌሎች የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሰነዶች ሕዝብ እንዲያውቃቸው መደረግ እና ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ መንገድ መያዝ አለባቸው፡፡

## ፰ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ኃላፊነት

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ስለሚያከናውኑት ግዥ እና ስለሚያስተዳድሩት ንብረት ጠቅላላ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፣ በተለይም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ ከሚገለፁት ዝርዝር ኃላፊነቶች በተጨማሪ የሚከተሉት አጠቃላይ ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

4. Accountability for decisions made and measures taken with regard to public procurement and property administration;

5. Careful handling and proper use of public property.

## *6. International Obligations*

1. To the extent that this proclamation conflicts with an obligation of the City Government under or arising out of an agreement with one or more other states or with an international organization, the provisions of that agreement shall prevail.
2. Where an agreement referred to in sub-article (1) of this Article contains a preference or preferences in favor of national and resident bidders, the public body shall ensure that the applicable preference or preferences are clearly stated in the bidding document.

## *7. Public Accessibility of Legal Texts*

This Proclamation and the procurement and property directives to be issued by the Bureau as well as other documents pertaining to public procurement and property administration shall be promptly made accessible to the public and systematically maintained.

## *8. Responsibilities of Heads of Public Bodies*

Public bodies shall have overall responsibility for procurements they carry out and the property they administer. In particular, the head of a public body shall apart from those specified in the directives to be issued by the Bureau, have the following responsibilities:-

ሀ) በተገቢው የሰው ኃይል የተሟላ የፋይናንስ ግዥና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ተግባራትን የሚያከናውን የሥራ ክፍል ያደራጃል፣

ለ/ በግዥ እና በንብረት አስተዳደር ሥራ ላይ የሚመደቡ ወይም የተመደቡ ሰራተኞች ይህንን አዋጅ ፣ የአፈፃፀም መመሪያውን ፣ የግዥ ማኑዋል፣ መደበኛ የጨረታ ሰነድ እና ሌሎች ተገቢ ቅፆች ይዘት እና አጠቃቀም እንዲያውቁ ማድረግ የሚያስችል ስልጠና ማግኘታቸውን እና የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደርን ለመፈፀም በቂ ክህሎት ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣

ሐ/ የመንግስት ግዥ በእቅድ ላይ የተመሰረተ እና በዚህ አዋጅ የተመለከቱ የግዥ መርሆ-ዎችን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፣

መ/ የፋይናንስ የግዥና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ተግባራቸውን በተገቢው ሁኔታ መወጣታቸውን ያረጋግጣል፣

ሠ/ እንደ አስፈላጊነቱ የግዥ ሥርአትን የሚያስፈፅሙ ሦስተኛ ወገኖችን ይቀጥራል፣

ረ/ የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣

ሰ/ በመ/ቤቱ ሥር የሚገኘው የመንግሥት ንብረት በሚገባ የተመዘገበ እና የክትትል ሥርዓት የተዘረጋለት፣ ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገለት፣ አገልግሎት የማይሰጥ ሆኖ ሲገኝ በወቅቱ እንዲወገድ መደረጉን ያረጋግጣል።

a) Cause to be established an adequately staffed unit for procurement and property administration;

b) ensure that staff and officials assigned in the procurement and property administration and those assigned as members of the procurement endorsing committee receive training to enable them acquire knowledge of the content and application of this Proclamation, the directives to be issued in accordance with this Proclamation, the procurement and property administration manuals, the standard bidding documents and other relevant forms;

c) Ensure that the procurement of the public body is preplanned and complies with procurement principles enshrined in this Proclamation;

d) Ensure that the finance, procurement and property administration core process properly discharge their functions;

e) Where necessary, enter into a contract with third parties which support the public body in the process of procurement;

f) Ensure that property at the disposal of the public body is used in such a manner as to achieve economy and efficiency;

g) Ensure that properties within the public body are properly recorded and follow up procedures are established, appropriately protected and preserved, timely disposed in case they become out of use.

**፱ የፋይናንስ የግዥና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ተግባርና እና ኃላፊነት**

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚቋቋመው የፋይናንስ የግዥና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት በግዥ መመሪያና በመሥሪያ ቤቱ በሚዘጋጀው የሥራ ዝርዝር ከሚሰጡት ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉት አጠቃላይ ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ/ የመንግስት ግዥን በተሟላ የሙያ ስነ ምግባር እና ክህሎት ይፈፅማል

ለ/ ይህንን አዋጅ፣ የአፈፃፀም መመሪያውን ፣ የግዥ ማኑዋል ፣ መደበኛ የጨረታ ሰነድ እና የአፈፃፀም ቅፆችን እና የግዥ ውሉን መሠረት በማድረግ የመንግሥት ግዥን ይፈፅማል::

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፭ በተደነገገው መሰረት ለየግዥው የተሟላ መረጃ ይይዛል፣ በተጠየቀ ጊዜም ያቀርባል::

**፲. ተጠያቂነት**

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሥራ የተመደቡ ሠራተኞች ወይም የመንግሥት ግዥን እና ንብረትን ለማስተዳደር የተሾሙ ኃላፊዎች በዚህ አዋጅ እና የቢሮ ኃላፊ በሚያወጧቸው መመሪያዎች መሠረት ስለሚወስዷቸው እርምጃዎች ተጠያቂ ይሆናሉ::

## ምዕራፍ ሁለት
## የቢሮው ሥልጣንና ኃላፊነት

**፲፩ .<u>የቢሮው ዓላማዎች</u>**

ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የቢሮው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው:-

፩. ፍትሃዊ፣ በውድድር ላይ የተመሠረተ፣ ግልፅ፣ አድልዎ የሌለበት፣ ለመንግሥት ገንዘብ ተመጣጣኙን ዋጋ ማስገኘት የሚያስችል የግዥ አፈፃፀምና ዘመናዊ የመንግስት ንብረት አስተዳደር መኖሩን ማረጋገጥ፣

**9. *Functions and Responsibilities of Procurement and property Administration Core Process***

The procurement core process in a public body shall, apart from the responsibilities assigned to it by the procurement directives and the job description prepared by the public body have the following functions and responsibilities.

a) Execute public procurement in a perfectly ethical and skillful manner,

b) carry out public procurement in accordance with this Proclamation, the procurement directives, the procurement manual, the standard bid documents, the forms and the procurement contract;

c) Maintain complete record for each procurement in accordance with Article 15 of this proclamation.

**10. *Accountability***

Procurement and property administration staff or heads of procurement and property administration units and members of the procurement endorsing workers in public bodies shall be accountable for their actions in accordance with this proclamation and the directives to be issued by the Head of Bureau.

## <u>CHAPTER TWO</u>
## <u>POWER AND RESPONSIBILITIES OF THE BUREAU</u>

**11. Objectives of the Bureau**

For the purpose of implementation of this Proclamation, the objectives of the Bureau shall be to:-

1. Ensure the application of fair, competitive, transparent, non-discriminatory and value for money procurement and modern public property administration;

፪. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር ተግባራት በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩትን ጠብቀው መሥራታቸውን መከታተል፣

፫. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ያለውን የግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አስተዳደር አቅም ማሳደግ፣

፬. በከተማ ደረጃ የተጣጣመ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ስርዓት እንዲኖር ጥረት ማድረግ፣

፭. የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ስርአት ተቀባይነት ካላቸው አለም አቀፍ ስርአቶች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ጥረት ማድረግ፣

## ፲፪. የቢሮው ተግባሮች

ቢሮው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባሮች ያከናውናል:-

፩. በመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ፖሊሲዎች፣ መርሆዎችና አፈፃፀሞች ላይ አስተዳደሩን የማማከር፣ ለአስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣

፪. በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ያለውን የመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ተግባራዊነት መከታተል፣ ለአስተዳደሩ ሪፖርት ማድረግ እና በሕግና በአፈፃፀም ሥርዓቱ ላይ የማሻሻያ ሀሣቦች ማቅረብ፣

፫. አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ሥልጠና እንዲሁም የግዥና የንብረት አስተዳደር አፈፃፀምን ለመምራት የሚያስፈልገው ችሎታ፣ በሙያው ለመሠማራት ተፈላጊ የሆነው ማስረጃ ዓይነት እና የሙያው ዕድገት ሊከተል የሚገባው ሂደት መወሰኑን ማረጋገጥ፣

፬. መደበኛ የግዥ ሰነዶች፣ አሠራሩን የሚመሩ ቅፆች እና ሌሎች ለግዥ እና ንብረት አስተዳደር አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች ማዘጋጀት፣ ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣

2. Follow up compliance of public bodies with the provisions of this proclamation in conducting procurement and administration of property at their disposal;

3. Build the capacity of procurement and property administration within the Addis Ababa City Government;

4. Work for the prevalence of uniform and consistent system of public procurement and property administration at City level;

5. Endeavor to harmonize the system of public procurement and property administration with the internationally recognized standards.

## 12. *Functions of the Bureau*

The functions of the Bureau are to:-

1. advise the City Government on all public procurement and property administration policies, principles and implementation and provide technical assistance to the public bodies of the City Government;
2. monitor and report to the City Government the performance of the public procurement and property administration systems in the City Government, initiate amendments on laws and implementation system improvements:
3. in collaboration with competent authorities ensure the setting of training standards, competence levels, certification requirements and professional development paths of public procurement and property administration.
4. prepare, update and issue authorized versions of the standard bidding documents, procedural forma and any other attendant documents pertaining to procurement and property administration.

፭. ከተፈቀዱ መደበኛ የግዥ ዘዴዎች፣ ሰነዶች፣ አሠራሩን ከሚመሩ ቅፆች እና ሌሎች ለግዥ አፈፃፀም አግባብነት ካላቸው ሰነዶች ውጪ ግዥ ለመፈፀም ወይም ከተፈቀዱ የንብረት አወጋገድ ሥርዓቶችና ስልቶች ውጭ ንብረት ለማስወገድ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጥያቄ ሲቀርብለት ጥያቄውን መርምሮ ውሣኔ መስጠት፡፡

፮. በመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ ፍላጐት ያላቸው አቅራቢዎች የሚመዘገቡበትን የተቀላጠፈ ሥርዓት መዘርጋት፣ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ለመመዝገብ የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን መቀበል፣ መመርመር እና መመዝገብ፣ እና የምዝገባውን ዝርዝር ማሠራጨት፣

፯. በዕጩ ተወዳዳሪዎችና በአቅራቢዎች ላይ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚያቀርቧቸውን አቤቱታዎች መርምሮ ውሣኔ መስጠት፣ የውሣኔውን ቅጂ ለሚመለከታቸው ማሠራጨት፣

፰. ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር ባደረጉት የግዥ ውል መሠረት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው፣ ስለብቃታቸው ሀሰተኛ መረጃ በማቅረባቸው ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫(፫) እና ፳፬(፪) የተዘረዘሩትን ድርጊቶች በመፈፀማቸው ምክንያት በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እንዳይሳተፉ ያገዳቸውን አቅራቢዎች ዝርዝር መያዝና ማሠራጨት፣

፱. የግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አስተዳደር ተግባራት ይህንን አዋጅ እና ሌሎች የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር የሚመራባቸውን ሰነዶችን ጠብቀው የተከናወኑ መሆኑን ለማረጋገጥ የግዥ ኦዲት ማድረግ፣

፲. ለግዥ አፈጻጸም እና ንብረት አስተዳደር የሚያገለግል የመረጃ ማስረጃ እና ክምችት ማቋቋም፣ ማጐልበት፣ መጠበቅ እና ወቅታዊነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፣

፲፩. የተቋም እና የሰው ኃይል አቅም ለማጐልበት የሚያስችል የአቅም ግንባታ ፖሊሲና ዕቅድ እንዲኖር ማድረግ፣

5. consider and decide on request from public offices to deviate from the prescribed methods of procurement, the standard bidding documents, procedural forms and any other attendant documents in effecting procurement or use other systems or methods of disposing of public property than those authorized by law,

6. introduce an efficient system of listing under which suppliers who are interested to participate in public procurement are registered; receives, reviews and records applications by candidates for registered supplier status and distribute the suppliers list,

7. review and decide on complaints submitted by public bodies on the conduct of bidders or suppliers, and send copies of such decision to the concerned organs;

8. maintains and distributes a list of suppliers who by reason of having seriously neglected their obligations under a public procurement contract, or having provided false information about their qualifications or having committed the act of the kind referred to in Article 13(3) and 24 (2) of this proclamation have been debarred from participating in public procurement by the Agency;

9. conduct audit to ensure that procurement and property administration activities of public bodies are in accordance with this proclamation and other documents governing public procurement and property administration:

10. set up, develop, maintain and update a date base that covers the entire spectrum of public procurement and property administration:

11. develop policies and maintain an operational plan on capacity building both for institutional and human resource development:

፲፪ የሙያና ከሙያ ጋር በተያያዙ አግባብነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የተሠማሩ ሆነው በመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ለመሳተፍ ፍላጐት ካላቸው አካላት ጋር ተቋማዊ ግንኙነት መፍጠር እና ማጳበር፣

፲፫. ስለመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አስተዳደር ጥናት ማካሔድ፣የአቅም ግንባታ ትብብር እንዲኖር ማድረግ፣

፲፬. ይህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም በአስተዳደሩ የተሰጡት ሌሎች ተግባሮች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፣

፲፭. ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚቀርብለትን መረጃ መሠረት በማድረግ የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት በሚገባ የሚሠራ ስለመሆኑ ለከንቲባዉ የሩብ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርት ማቅረብ፣ ከንቲባዉ በሚጠይቀው ዝርዝር መሠረት በእያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ስለተከናወነው ግዥ ዓይነት እና መጠን እንዲሁም ንብረት አስተዳደር ጉዳዮች ልዩ መረጃዎችን መስጠት፣

፲፮. በዚህ አዋጅ በመንግስት ግዥ አፈጻጸምና ንብረት አወጋገድ ላይ በዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ዉሳኔ መስጠት፣

፲፯. ከፌደራል የግገር ኤጀንሲ እና አግባብነት ባላቸው የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት አካላት የመንግስት አካላት ግዥ አፈጻጸም ላይ እንዳይሳተፍ የታገደ እጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ በከተማ አስተዳደሩ መንግስት መሥሪያ ቤቶች ግዥ እንዳይሳተፍ ማድረግ፣

፲፰ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት ላይ ለሚውሉ ዋና ዋና ቋሚ ንብረቶች ደረጃ ማውጣት፣ አፈጻጸሙን መከታተል፣

12. Establish and maintain institutional linkages with entities working for the development of a profession and related matters who have an interest to participate in public procurement

13. undertake public procurement execution property administration research and survey and establish cooperation in the area of capacity building;

14. Administer and enforce compliance with all the provisions of this proclamation, regulations and directives to be issued in accordance with this proclamation, and other functions given to it by the Bureau;

15. Submit quarterly and annually report to the Mayor regarding the overall functioning of the public procurement and property administration system based on information provided to it by public bodies and provide such data as the Mayor may request regarding the nature and volume of public procurement handled by each entity: as well as on matters of property administration;

16. Provide decisions for complaints of candidates on the issues raising from these proclamation concerning public procurement and disposal of public property;

17. cause not participate, any supplier barred by the decision of competent authorities of the Federal Procurement Agency and other Regional Government organs, in any procurement of the City Government;

18. Set a standard for major items of public bodies representing important fixed assets and follow-up adherence to such standards.

፲፫ የቢሮው ሥልጣን

የአስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣዉ በተሻሻለዉ አዋጅ ቁጥር ፲፭/፪ሺህ፩ ን መሰረት ለቢሮው የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣን ይኖረዋል:-

፩. ማናቸውም የመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም አቅራቢ ሕግ ከሚያዘው ውጪ ስለመፈፀሙ፣ ግዥ በትክክል ስላለማከናወኑ፣ የግዥውን አሠራር በትክክል ስላለመፈፀሙ ወይም ስለመመሳጠሩ ጥቆማ የቀረበ እንደሆን ከግዥው አፈፃፀም ጋር የተያያዙ መረጃዎች፣ ሰነዶች መዝገቦች እና ሪፖርቶች እንዲቀርቡለት የማዘዝ፣

፪ . ምስክሮችን የመጥራት፣ ምስክሮችና ግዥው የሚመለከታቸው ወገኖች ቃላቸውን በመሀላ እንዲሰጡ የማድረግ፣ የሂሳብ መዝገብ፣ ፕላን፣ ሰነድ እንዲቀርብለት የማድረግ፣

፫. ከገበያ ጋር የማይጣጣም ዋጋ በሚያቀርቡ እና ሌሎችንም የዚህን አዋጅ እና በቢሮ የሚወጣውን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረኑ ተግባራት የሚፈፅሙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች፣ አቅራቢዎች ወይም በመንግሥት ንብረት ማስወገድ ሂደት ተሳታፊዎች ላይ በቀረበ አቤቱታ መነሻነት ማስጠንቀቂያ የመስጠት፣ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ በመንግሥት ግዥ ወይም የንብረት ማስወገድ ሂደት እንዳይሳተፉ የማገድ፣

፬. በመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አፈፃፀም ላይ በራሱ ፕሮግራም ወይም በሚደርሰው ጥቆማ መነሻነት ኦዲት እንዲካሄድ ማድረግ፣

፭. በቂ ምክንያት ያለ መሆኑን ሲረዳ በዚህ አዋጅና በግዢ መመሪያው ከተፈቀዱ የግዢ ሥርዓቶች ውጪ ግዥ ለመፈፀም ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መሠረት እንዲፈፀም መፍቀድ፣

*13. Powers of the Bureau*

Notwithstanding to the powers given to the Bureau by the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Services Organs Re-establishment Proclamation No. 15/2009, the Bureau shall have the power to:

1. Require any information, documents, records and reports in respect of any aspect of the public procurement process where a breach, wrongdoing mismanagement or collusions has been alleged, reported or proven against any public body.
2. summon witnesses, call for the production of books of accounts, plans, documents and examine witnesses and parties concerned on oath;
3. give warning to or suspend for a definite or indefinite period of time from participating in public procurement candidates, suppliers or persons involved in the disposal of public property where it proves that they have offered a price higher than the market or committed an act contravening the provisions of this proclamation and the directives to be issued by the Bureau;
4. conduct audit on its own program or cause audit to be conducted where it receives allegations of misconduct warranting such audit on a process of public procurement and property administration;
5. Upon the request of public bodies, exceptionally and Justified on sound grounds, may permit the use of a procedure which is not consistent with the procedures laid down by this proclamation or the procurement directive.

## ምዕራፍ ሦስት
## መሠረታዊ የግዥ ድንጋጌዎች

**፲፬. የግዥ ዕቅድ**

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በበጀት ዓመቱ የሚፈፅሙትን ግዥ የሚያሳይ እና ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ የሚገለፁትን ዝርዝር ጉዳዮች ያካተተ ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የተዘጋጀው የግዥ ዕቅድ በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ፀድቆ ለሚመለከታቸው የመ/ቤቱ የሥራ ክፍሎች እና ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በየዓመቱ እስከ ሐምሌ ፴ መላክ ይኖርበታል፡፡

**፲፭. <u>የግዥ ሰነዶች</u>**

፩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከመንግሥት ግዥ ጋር የተያያዙ መዝገቦችን እና ሰነዶችን ግዥው ከተፈፀመበት ቀን አንስቶ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ እስከሚገለፀው ጊዜ ድረስ ማቆየት አለባቸው፡፡ በዚህ ዓይነት የሚያዙት መረጃዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡፡

ሀ/ የሚገዙትን ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች አጭር መግለጫ፣

ለ/ የጨረታ ማስታወቂያ፣

ሐ/ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ወይም የዋጋ ማቅረቢያ ያቀረቡ አቅራቢዎች ስምና አድራሻ እንዲሁም በጨረታው አሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ስምና አድራሻ፣

መ/ ለጨረታ ግምገማ የተዘጋጀውን መስፈርት እና ተፈፃሚ የተደረገበትን ሁኔታ፣ የጨረታ ግምገማና የውድድሩን አፈፃፀም እና ከተወዳዳሪዎች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሀሳብ እና የዋጋ ማቅረቢያ የሚያሳይ አጭር መግለጫ፣

ሠ/ አቤቱታ ቀርቦ ከሆነ የውሣኔ አሰጣጥ ሒደቱን የሚያሳይ መረጃ፣

ረ/ ከግልፅ ጨረታ ውጪ ሌሎች የግዥ ዘዴዎች መከተል የተመረጠበትን ምክንያት፣

## CHAPTER THREE
## BASIC PUBLIC PROCUREMENT PROCEDURES

**14. *Procurement Plan***

1. Public bodies shall have to prepare an annual procurement plan showing their procurement for the concerned budget year and containing such details as are stated in the directive to be issued by the Bureau.
2. The procurement plan to be prepared in accordance with sub-article (1) of this Article shall have to be reported to the concerned public bodies and The Finance and Economic Development Bureau until Hamle 30 of the Ethiopian Calendar.

***15.* Records of Procurement**

1. Public bodies shall have to maintain records and documents regarding their public procurement for such period of time as is determined by the directive to be issued by the Bureau from the date of concluding any procurement proceeding. Such information shall include the following:-

   a. A brief description of the goods works or services to be procured;

   b. The invitation to bid;

   c. The names and addresses of suppliers that submitted bids, proposals or quotations, and the name and address of the wining suppliers;

   d. The evaluation criteria stipulated and applied and a summary of the evaluation and comparison of bids, proposals and quotations received;

   e. Information on the proceeding of any decision rendered where a complaint against procurement process is lodged;

   f. The grounds for using a procurement procedure other than open bidding.

፪ ከአሸናፊው ጋር ውል ከተፈረመ ወይም በማናቸውም ምክንያት ውሉ ከተቋረጠ በኋላ የግዥውን ዝርዝር አፈፃፀም የሚያሳየው መረጃ በጨረታው ዕጩ ተሳታፊ የሆኑ ተወዳዳሪዎች ሲጠይቁ እንዲያዩት መደረግ አለበት:: ይሁን እንጂ በሕግ ሥልጣን በተሠጠው አካል ወይም ፍ/ቤት ካልታዘዘ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሚከተሉትን መረጃዎች መስጠት የለበትም::

ሀ/ የመረጃው ይፋ መሆን በሕግ የማይፈቀድ፣ የሕግ አፈፃፀምን የሚያሰናክል፣ የሕዝብን ጥቅም የሚቃረን፣ የተዋዋዮችን ሕጋዊ የንግድ ጥቅም እንዲሁም ቀና ውድድርን የሚጐዳ ከሆነ፣

ለ/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) (መ) በተመለከተው መሠረት በማሳጠር የተዘጋጀውን ሰነድ ካልሆነ በስተቀር ከተጫራቾች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሀሳብ ከመመርመር እና ከመገምገም ተግባር ጋር የተያያዙ መረጃዎችን፣ እና ተጫራቾች ያቀረቡዋቸውን የመወዳደሪያ ሀሳቦች እና የጨረታ ሰነዶች ይዘት የሚገልፁ መረጃዎች፣

## ፲፮. አድልዎ ያለማድረግ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዜግነት፣ በዘር ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም ሂደት በማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ላይ አድልዎ ሊደረግ አይችልም::

## ፲፯ ልዩ አስተያየት

፩. ቢሮው በሚወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሠረት በጨረታ ግምገማ ወቅት በኢትዮጵያ ለተመረቱ ዕቃዎች፣ በኢትዮጵያ ኩባንያዎች ለሚከናወኑ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች እና በኢትዮጵያ ኩባንያዎች ለሚከናወኑ የምክር አገልግሎት ሥራዎች ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል::

፪. በአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማት አዋጆች መሠረት የተቋቋሙ አነስተኛ ተቋማት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮ ኃላፊዉ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተጨማሪ ልዩ አስተያየት ሊደረግላቸው ይችላል::

2. The record concerning any proceeding shall on request, and once the proceedings have resulted in a contract or have otherwise been terminated are made available to candidates who participated in the proceedings. However, except when ordered to do so by a competent court or other body authorized by law and subject to the conditions of such an order, the public body shall not disclose:

a. information if its disclosure would be contrary to law, would impede law enforcement, would not be in the public interest, would prejudice legitimate commercial interest of the parties or would inhibit fair comptetion

b.information relating to the examination and evaluation of bids, proposals or quotations and the actual content of bids, proposals or questions, other than in the summary record form referred to in sub-article (1)(d) of this Article.

## *16. Non-discrimination*

Without prejudice to the provisions of Article 16 of this Proclamation, candidates shall not be discriminated against in the proceeding of public procurement on the basis of nationality, race or any other criterion not having to do with their qualifications.

## 17. *Preference*

1. A preference margin which shall be determined by a directive to be issued by Bureau for goods produced in Ethiopia, for works carried out by Ethiopian nationals and for consultancy services rendered by Ethiopian nationals be granted in the evaluation process.
2. In addition to the preference provided for in sub-article (1) of this Article, further preference of such margin as to be determined by the directive to be issued by the Head of Bureau may be allowed for small and micro institutions.

፫. የዕቃዎች፣አገልግሎቶች ወይም የግንባታ ሥራዎች ጥራትና ዋጋ ተመሳሳይ ሆኖ ተጫራቾች በግምገማ እኩል ነጥብ ሲያገኙ ለአገር ውስጥ ምርቶች፣አገልግሎቶች ወይም ኩባንያዎች ቅድሚያ ይሰጣል

፬. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አፈፃፀም ማናቸውም ዕቃ ከዋጋው ከ፴፭ መቶኛ በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ ከሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተመረተ ይቆጠራል።

፲፰. የግንኙነት ስልት

፩ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች በጽሑፍ መደረግ አለባቸው። በጽሑፍ ያልተደረጉ ማናቸውም ግንኙነቶች በመከታተል በጽሑፍ መረጋገጥ አለባቸው።

፪. የቢሮ ኃላፊ የመረጃ ልውውጡን ትክክለኛነት እና በምስጢር መጠበቁን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥርዓቶች መዘርጋታቸውን እና በቴክኒክ ረገድ ተፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ከጽሑፍ በተጨማሪ ወይም በጽሑፍ ምትክ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ግንኙነት ማድረግ የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፲፱. ቋንቋ

፩. ዓለም አቀፍ ተጫራቾች የሚሳተፉበት ግዥ ካልሆነ በስተቀር የአገር ውስጥ ተጫራቾች ብቻ ለሚሳተፉበት ብሔራዊ ጨረታ የጨረታ ሰነድ የሚዘጋጀው እና ጨረታው የሚካሔደው በአማርኛ ቋንቋ ነው። ሆኖም ለግዥው አካሔድ አመቺ መሆኑ ከታመነበት የተሟላ ውድድርን እንደማይገድብ ተረጋግጦ የአገር ውስጥ ተጫራቾች ለሚሳተፉበት የአገር ውስጥ ጨረታ፣ የጨረታ ሰነድ እና የመጫረቻው ሰነድ በእንግሊዘኛ ቋንቋ እንዲዘጋጁ የመንግሥት መ/ቤቱ ሊፈቅድ ይችላል።

፪. ለዓለም አቀፍ ግዥ ጨረታ ማስፈፀሚያ የሚዘጋጁት ማናቸውም ሰነዶች በእንግሊዘኛ ቋንቋ መሆን ይኖርባቸዋል።

3. Where in the evaluation of bids for procurement of goods, services or works equal percentage points are resulted for bidders offering similar price and quality, preference shall be given to local goods, services or companies.

4. For the purpose of sub-article (1) of this Article any good to which more than 35% of the value added occurs in Ethiopia shall be deemed as one which is produced in Ethiopia.

**18. *Form of Communications***

1. Communications between candidates and public bodies shall be in writing; any communications not made in written form shall be subsequently referred to and confirmed in writing.
2. Subject to necessary safeguards with regard to authenticity and confidentiality, and when technical conditions so permit, the Head of Bureau may issue a directive to determine the extent by which communication by electronic means may be used in addition to or instead of writing.

***19. Language***

1. Except where a procurement proceeding involves international bidders, for national bids in which only local bidders participate, the bid document shall be prepared and the bid document shall be conducted in the Amharic language. However, if it is found to facilitate the procurement process, the use of English language in the preparation of bid documents and bid proposals in a national bid in which only local bidders participate, provided that such an act is not prejudicial to fair competition.
2. For procurement to be conducted by means of international competitive bidding, all documents shall have to be prepared in English language.

## ፳ የዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቃት

፩. በማንኛውም የመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከግዥው ልዩ ባህርይ በመነሳት የሚያወጧቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው::

ሀ/ በሚገቡት ውል መሠረት ለመፈፀም የሚያስችል የሙያና የቴክኒክ ብቃት፣ የፋይናንስ አቅም፣ መሣሪያ እና ሌሎች የመገልገያ ሥፍራዎች፣ ግዥው በሚፈፀምበት ተግባር የሥራ አመራር ችሎታ፣ መልካም ዝና እና የሰው ኃይል ያላቸው፣

ለ/ ውል ለመፈፀም የሚያስችል የሕግ ችሎታ ያለው፣

ሐ/ በዕዳ ያልተያዘ፣ ያልከሠረ ወይም የሥራ እንቅስቃሴውን ያላቋረጠ፣ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ያልታገደ፣ ወይም በእነዚህ ምክንያቶች ተከሶ በክርክር ላይ ያልሆነ፣

መ/ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበ፣

ሠ/ በመንግስት ግዥ እንዳይሳተፍ ታግዶ የነበረ ከሆነ የታገደበትን ጊዜ ያጠናቀቀ፣

ረ/ የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለውና በኢትዮጵያ የግብር ሕጐች በተደነገገው መሠረት የግብርና የታክስ ግዴታውን የተወጣ፣

ሰ/ የባንክ ሂሳብ ያለው፣

፪. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ የሰነድ መረጃዎችን ወይም ሌሎች መረጃዎችን እንዲያቀርቡ መጠየቅ ይችላል::

፫. በዚህ አንቀጽ መሠረት ዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲያሟሉ የሚጠበቁት መስፈርቶች በጨረታ ሰነድ ወይም የተጫራቾችን የመወዳደሪያ ሀሳብ ለመጠየቅ በሚዘጋጁ ሰነዶች ውስጥ መመልከት ያለባቸው ሲሆን፣ በሁሉም ተጫራቾች ላይ በእኩልነት ተፈፃሚ መሆን አለባቸው::

፬. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የሚቀርቡትን ሰነዶች እና

## 20. *Qualification of Candidates*

1. In order to participate in public procurement, candidates must qualify by meeting the following criteria and such other criteria, as the public body considers appropriate under the circumstances:-
   a. that they possess the necessary professional and technical qualifications and competence, financial resources, equipment and other physical facilities, managerial capability, experience in the procurement object, reputation, and the personnel, to perform the contract;
   b. that they have the legal capacity to enter into the contract;
   c. that they are not insolvent, in receivership, bankrupt or being wound up, their business activities have not been suspended, and they are not the subject of legal proceedings for any of the foregoing;
   d. subject to the directives to be issued by the Bureau, that they are registered in the suppliers list;
   e. that the period for which they were suspended from participating in public procurement is over;
   f. that they have renewed trade license and fulfilled their obligations to pay taxes according to Ethiopian tax laws;
   g. that they have a bank account.
2. The public body may require candidates to provide such appropriate documentary evidence or other information as it may been useful to satisfy itself that the candidates are qualified in accordance with the criteria referred to in sub-article (1) of this Article.
3. Any requirement established pursuant to this Article shall be set forth in the bid documents or other documents for solicitation of proposals, and shall apply equally to all
4. The public body shall evaluate the qualifications of candidates in accordance with the criteria and

የመመዘኛ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ብቃት መገምገም አለበት፡፡

፭. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ብቃት ያላቸው መሆኑን ለማስረዳት ሀሰተኛ መረጃ የያዙ ሰነዶችን ያቀረቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ብቃታቸውን ለማረጋገጥ ያቀረቡት መረጃ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ወይም ያልተሟላ መሆኑ በማናቸውም ጊዜ የተረጋገጠ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከጨረታ ውጪ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

**፳፩ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ**

፩. ስለግዥው ምንነት ትክክለኛና የተሟላ መግለጫ እንዲኖር እንዲሁም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ፍትሀዊና ግልፅ በሆነ አሠራር መወዳደር የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ግዥ ፈፃሚ አካላት የሚገዙዋቸውን ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች ባህርይ የሚያሳይ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

፪. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው የመንግስት መ/ቤቱ ሊገዛ የሚፈልገውን ዕቃ ጥራት፣ ጠቀሜታ፣ ተገቢ ጥንቃቄ፣ እንደአስፈላጊነቱ መለኪያውን፣ መለያውን፣ መጠሪያውን፣ አስተሻሸጉን፣ ምልክቱን፣ ወይም የአመራረቱን ሂደትና ዘዴ እንዲሁም ተፈላጊ የሆነውን ባህርይ የሚያሟላ መሆኑ የሚረጋገጥበትን ሥርዓት የሚገልፅ መሆን አለበት፡፡

፫. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሚያዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ እስከተቻለ ድረስ፣

ሀ/ በዲዛይን ወይም ባሕሪያትን በመዘርዘር ላይ ሳይሆን በጠቀሜታ ላይ፣

ለ/ አገራዊ ደረጃ የወጣለት ሲሆን ደረጃውን ወይም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን ደረጃዎች ወይም የግንባታ ኮዶች መሠረት ያደረገ ፣

ሐ/ ሰፊ ውድድርን የሚጋብዝ እና ውድድርን ሊገድቡ የሚችሉ መግለጫዎች ያልተካተቱበት መሆን አለበት፡፡

፬. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ፍላጎት በትክክል ለመግለፅ አስቸጋሪ ካልሆነ ወይም ሌላ ዘዴ ካልታጣ በስተቀር የቴክኒክ መግለጫ የተለየ የንግድ ምልክት ወይም ስም፣ ፓተንት፣ ዲዛይን ወይም የተወሰነን አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ የሚጠቅስ መሆን የለበትም፡፡ አስገዳጅ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ «ወይም ተመሳሳዩን» የሚል ሐረግ በዕቃና አገልግሎት ዝርዝሩ ውስጥ መታከል ይኖርበታል፡፡

procedures set forth in the documents referred to in sub-article (3) of this Article.

5. The public body shall disqualify a candidate who submits a document containing false information for purposes of qualification; it shall disqualify a candidate if it finds at any time that the information submitted concerning the qualifications of the candidate was materially inaccurate or materially incomplete

***21. Technical Specification***

1. Technical specifications and descriptions laying down the characteristics of the goods, works or services to be procured shall be prepared for the purpose of providing a correct and complete description of the object of procurement and for the purpose of creating conditions of fair and open competition between all candidates.

2. The technical specifications shall clearly describe the public body's requirements with respect to quality, performance, safety and where necessary dimensions, symbols, terminology, packaging, marking and labeling or the purpose of creating conditions of fair and open competition between all candidates.

3. Technical specification prescribed by public bodies shall, as far as possible:
   a) be in terms of performance rather than design or descriptive characteristics;
   b) be based on national standards, where such exist, or otherwise on internationally recognized standards or building codes:
   c) inviting open competition and devoid of any statement having the effect of restricting competition.

4. There shall be no requirement or reference in the technical specifications to a particular trademark or name, patent, design or type, specific original way of describing the procurement requirements of the public body and provided that words such as "or equivalent" are included in the specifications.

**፳፪ ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሀሳብን እና የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ ስለማድረግ**

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከሚከተሉት በአንዱ ወይንም ከአንድ በላይ በሆኑ ምክንያቶች ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሀሳብን እና የዋጋ ማቅረቢያን የግዥ ስምምነት ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ማድረግ ይችላሉ፡፡

ሀ/ በግዥ አካሔዱ ላይ ውጤቱን ሊያዛባ የሚችል ስህተት መፈፀሙ ከተረጋገጠ፣

ለ/ በስራ ዕቅድ መቀየር ምክንያት ወይም የመሥሪያ ቤቱን ፍላጎቱን ለማሟላት ሌላ የተሻለ አማራጭ በመፈጠሩ ምክንያት ግዥውን ማካሔድ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የተሻለ ቴክኒካል ወይንም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሐ/ የቀረቡት ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርት የማያሟሉ ሲሆን ፣

መ/ በጨረታ የቀረበው ዝቅተኛ ዋጋ ከገበያ ዋጋ በላይ ሲሆን፣ እና የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ድጋሚ ጨረታ በማውጣት የተሻለ ዋጋ የሚገኝ መሆኑን ሲገምት፣

ሠ/ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ተጫራች የሰጠው ዋጋ የግዥ ፈፃሚ መ/ቤቱ ለግዥው ከያዘው በጀት በላይ ሲሆን እና ባለበጀት መ/ቤቱ የበጀቱን ልዩነት ከሌላ ምንጭ ማሟላት የማይችል ሲሆን ፣

ረ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የግዥ አካሔዱን ለማዛባት በመመሳጠራቸው በቂ ውድድር አለመደረጉ ሲረጋገጥ፣

፪. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ ፩ በተመለከተው መሠረት ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሀሳብን ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል ሲሠርዙ ምክንያቱን የሚገልፅ ማስታወቂያ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ወዲያውኑ እንዲደርስ ማድረግ አለባቸዉ ፡፡ ሆኖም የምክንያቶቹን አግባብነት እንዲያስረዱ አይገደዱም፡፡

፫. ጨረታውን ውድቅ የማድረጉ ውሣኔ የተሰጠው ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ከሆነ የመጫረቻ ሰነዶቹ እንደታሸጉ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች መመለስ አለባቸው፡፡

**22. Rejection of Bids, Proposals and Quotations**

1. Public bodies may for one or more of the following reasons reject in whole or in part bids, proposals or quotations at any time prior to the conclusion of procurement contract where:
   a) there is proof of error in the procurement proceeding which could affect the outcome of the bid;
   b) it is ascertained that the procurement has no use in enabling the public body to obtain a better technical or economic advantage as a result of a change of work plan or another alternative representing a better option to meet the requirement of the public body;
   c) bidders fail to meet the minimum criteria set forth in the bid document;
   d) the minimum price offered in the bid does not match with the market price circulated by the Agency and the public body expected that it can get a better price advantage by re-advertising the bid;
   e) the price offered by the successful bidder exceeds the budgetary allocation made for the procurement and the public body cannot make up for the deficiency from any other source;
   f) it is proved that the bidding is not sufficiently competitive as a result of Connivance among candidates.
2. Public bodies shall have to give notice to candidates forth with disclosing the reasons for rejecting bids, proposals or quotations wholly or partially in accordance with sub-article (1) of this Article. However, they shall not be required to justify the reasons.
3. If the decision to reject all bids results before the opening date and time, the bids received shall be returned unopened to the candidates submitting them.

፬. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከዚህ በላይ በንዑስ አን ቀጽ ፩ በተመለከተው መሠረት ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሀሳብን ውድቅ በማድረጋቸው ምክንያት ምንም ዓይነት ተጠያቂነት አይኖርባቸውም፡፡

**፳፫ የኤሌክትሮኒክስ ግዥ**

ቢሮዉ ግዥ ወጪ ቆጣቢ ፣ ግልፅ እና ዘመናዊ እንዲሆን ለማድረግ እንዲቻል ሂደቱ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ እንዲፈፀም ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህንን ሥራ ላይ ማዋል እንዲቻል፡-

፩. ቢሮዉ ሀገሪቱ ለምትገኝበት የዕድገት ደረጃ ተመጣጣኝ የሆነ ግዥን በኤሌክትሮኒክ የመረጃ ልውውጥ ዘዴ የመፈፀም አሰራርን በማጥናት ያቀርባል፡፡

፪. ቢሮዉ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ፣ አቅራቢዎች እና በተቆጣጣሪ አካሎች አሰራሩን ለመተግበር የሚያስችል አቅም መፈጠሩን ያረጋግጣል፡፡

፫. ቢሮዉ የቀረበውን በኤሌክትሮኒክ የመረጃ ልውውጥ ዘዴ ግዥን የመፈፀም አሰራር በመመርመር እና አጠቃላይ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና የአቅራቢ-ዎች አሰራር እና አቅም ግዥን በኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ልውውጥ ለመፈፀም ዝግጁ ነው ብሎ ሲያምን ተገቢውን የአሰራር ስርአት በመዘርጋት ሥርዓቱ በተወሰኑ ወይም በሁሉም የመንግስት ግዥዎች ተፈፃሚ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

**፳፬ የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሥነ-ምግባር**

፩. ዝርዝር አፈፃፀማቸው ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ የሚገለፅ ሆኖ በግዥና ንብረት አስተዳደር ሥራ ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች የሚከተሉትን የስነ ምግባር መርሆዎች ተከትለው ተግባራቸውን ያከናውናሉ፡፡

4. The procuring entity shall incur no liability towards candidates solely by virtue of its invoking sub-article (1) of this Article.

***23. Electronic Procurement***

To achieve economical, transparency and modernization in public procurement, the Bureau may authorize the use of electronic means as a method of procurement. In order to implement this:

1. the Bureau shall conduct a study and submit proposal on a system of conducting procurement by means of electronic exchange of information which is appropriate to the level of development of the Country;
2. the Bureau shall ensure that public bodies, suppliers and supervising entities develop the capacity required to implement the system;
3. upon due consideration of the proposed system of effecting procurement by means of electronic exchange of information and where he is satisfied that the overall system and capacity of public bodies and suppliers allows the carrying out of procurement through electronic exchange of information, the Head of Bureau may authorize the implementation of the electronic system in all or certain public procurement proceedings by establishing the appropriate framework for the operation of the proposed electronic system.

***24. Rules of Ethics in Public Procurement and Property Administration***

1. Subject to the details to be specified in the directive to be issued by the Head of Bureau, personnel engaged in public procurement or property administration shall have to observe the following rules of ethics in the discharge of their duties:

ሀ/ የተፈጠረ ወይንም ሊፈጠር የሚችል የጥቅም ግጭትን የማሳወቅ እና ራስን ከሒደቱ የማግለል፣

ለ/ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እና አቅራቢዎች እኩል የመወዳደር እና የመፈፀም እድል የመስጠት፣

ሐ/ በስራ አጋጣሚ ያወቃቸውን የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን እና የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ወይም የአቅራቢዎችን መረጃ በሚስጥር መጠበቅ፣

መ/ ስጦታ ወይም የሥራ ዕድል ወይም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት አለመቀበል፣

ሠ/ በስራ ሒደት ያወቃቸውን ሊፈጠሩ የታሰቡ ወይንም የተፈጠሩ የሙስና ተግባራትን ለሕግ አስፈፃሚ አካላት የማሳወቅ እና ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት የማገዝ፣

ረ/ ለሕዝብ ሀብትና ንብረት ተቆርቋሪ መሆን፣

፪ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ የመንግስት የግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አወጋገድን ሊያዛባ ከሚችል ከማንኛውም ተግባር ራሱን ማግለል አለበት። በዚህ አዋጅ ምዕራፍ አሥራ አራት የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ተግባር ወይም ውሣኔ ለማዛባት ወይም ከግዥው አፈፃፀም እና ንብረት አወጋገዱ ጋር በተያያዘ መ/ቤቱ ሊከተለው የሚገባውን አሠራር ለማስለወጥ በመደለያ መልክ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ማናቸውንም ዓይነት ስጦታ አለመስጠት ወይም ስጦታ ለመስጠት ቃል አለመግባት ወይም የሥራ ዕድል ወይም ሌላ ማናቸውንም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት አለመስጠት ፣

ለ. የመንግስት ግዥ አፈፃፀምን ወይንም ንብረት አወጋገድ ለማዛባት በማሰብ የሐሰት ማስረጃ አለማቅረብ ወይንም መግለፅ የነበረበትንመረጃ አለመደበቅ፣

a) the obligations to notify any actual or possible conflict of interest and isolate oneself from any processes involving such conflict;

b) to give candidates and suppliers equal opportunity of competition and performance;

c) keep in secret any confidential information concerning the public body, candidate or supplier which he/she came to know on account of his/her duty;

d) to reject any gift or offer of an employment opportunity or anything of monetary value or service;

e) to inform the imminent treats and corruptions which he had known in performing his duty to the executive organs and support those who fight with the corruption and mal practices

f) demonstrate concern to public resource and property;

2. Any candidate or supplier shall have to refrain from any act contravening the process of public procurement and property disposal. Without prejudice the provisions of Chapter Fourteen of this Proclamation, any candidate or supplier shall have the responsibility:-

a with an intention to influence the decision or action of the head or/staff member of the public body or persuade the public body to change its established practice of procurement and property disposal, not to give directly or indirectly gifts of any kind in the form of inducement, not to promise to give gifts, not to offer enlivenment opportunity or

b. with an intention to mislead a procurement proceeding not to present a falsified document or not to withhold information he/she should have disclosed;

ሐ/ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ከሌላ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር በመመሳጠር የሐሰት ውድድር አለማድረግ፣

መ/ በስራ ሒደት ያወቃቸውን ሊፈጠሩ የታሰቡ ወይንም የተፈጠሩ የሙስና ተግባራትን ለሕግ አስፈፃሚ አካላት የማሳወቅ እና ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት የማገዝ፣ኃላፊነት አለበት፡፡

## ፳፭. የግዥ ዘዴዎች

፩. በመንግስት ግዥ አፈጻጸም የሚከተሉት የግዥ ዘዴዎች ስራ ላይ ይውላሉ፡፡

ሀ/ ግልፅ ጨረታ

ለ/ በመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ

ሐ/ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግገር

መ/ ውስን ጨረታ /በውስን ጨረታ የሚፈፀም ግዥ/

ሠ/ ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ

ረ/ በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ

፪ በዚህ አዋጅ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፡፡

፫ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከግልጽ ጨረታ ዉጪ በሌሎች የግገር ዘዴዎች ግገር መፈጸም የሚችሉት በዚህ አዋጅ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ይሆናል፡፡

፬ በዚህ አዋጅ ወይም በግገር መመሪያው የተዘረጉ የግገር ስርአቶችን ለመሸሽ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በአንድነት ሊፈጽሙ የሚገባቸው የዕቃ፣ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዥዎች መከፋፈል የለባቸውም ፡፡

## ፳፮. የመንግሥትና የግል ሽርክና

ቢሮዉ የመንግሥትና የግል ሽርክና የሚመሰረትበትን ሁኔታ እና የሽርክናውን ዝርዝር አፈፃፀም የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

c) not to connive with another candidate in an act of false completion in order to get unfair advantages;

d) to report to the law enforcement agencies any intended or completed action of corruption which he came to know during the procurement proceedings and contribute to the effort to fight corruption and malpractice.

## 25. *Methods of Procurement*

1. The following methods shall be used in public procurement:
   a) Open Bidding;
   b) Request for Proposals;
   c) Request for Quotation;
   d) Restricted Tendering/procurement effected by restricted tendering;
   e) Direct Procurement
   f) ) Two stage Tendering
2. Except as otherwise provided in this proclamation, public bodies shall use open bidding as the preferred procedure of procurement.
3. Public bodies may use a method other than open bidding only where conditions for use of such other method stipulated under this proclamation are satisfied.
4. Public bodies shall not split procurement for a given quantity of goods, works or services with the intention of avoiding the preferred procurement procedure stated under this Proclamation or in the Procurement Directive.

## *26. Public private partnership*

The Bureau may issue directive prescribing the rules governing the formation of public private partnership and the modes of implementation of such partnership.

## ምዕራፍ አራት
## የግልፅ ጨረታ አፈጻጸም

**፳፯. የጨረታ ማስታወቂያ**

፩/ የጨረታ ማስታወቂያ የጨረታ ሰነዱ በተዘጋጀበት ቋንቋ በሚታተም እና አገራዊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ቢያንስ አንድ ጊዜ መውጣት አለበት።

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የጨረታ ማስታወቂያው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ ከተጠቀሰው በተጨማሪ በብሔራዊ የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ጣቢያ ማስታወቂያውን ሊያስነግር ይችላል።

፫/ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ለጨረታ ማቅረቢያ የሚሰጠው ጊዜ በግዥ መመሪያ ከሚወሰነው አነስተኛ የቀን ብዛት ያነሰ መሆን የለበትም።

**፳፰. የጨረታ ጥሪ**

የጨረታ ጥሪ ከሚከተሉት በተጨማሪ በቢሮዉ የሚወጣውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ መሠረት በማድረግ መዘጋጀት አለበት።

ሀ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ስምና አድራሻ፣

ለ/ የዕቃውን፣ የግንባታ ሥራውን እና የአገልግሎቱን አጭር መግለጫ፣

ሐ/ የጨረታውን ሰነድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች እና የጨረታ ሰነዱ የሚገኝበትን ቦታ፣

መ/ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ የሚቀርብበትን ቦታ እና የማቅረቢያውን የመጨረሻ ጊዜ፣

ሠ/ ጨረታው የሚከፈትበትን ቦታ እና ጊዜ እንዲሁም ተጫራቾች ወይም ተወካዮች ጨረታው ሲከፈት መገኘት የሚችሉ መሆኑን የሚገልፅ ማሳሰቢያ፣

## CHAPTER FOUR
## PROCEDURE OF OPEN TENDERING

**27. *Advertisements***

1. Invitation to bid shall be advertised in at least one times in a national news paper of general circulation which is published in the language the bidding document is prepared.
2. Where the public body finds it necessary, it may, in addition to the medium mentioned in sub article (1) of this Article, advertise the bid on a national radio and television.
3. The time allowed for preparation of bids shall not be less than the minimum number of days stated in the procurement directives.

**28. *Invitation to Bid***

Apart from containing the following particulars, the invitation to bid shall be prepared in accordance with the standard bidding document to be developed by the Bureau;

a) The name and address of the public body;

b) A brief description of the goods, construction works or services to be procured;

c) The means and conditions for obtaining the bidding documents and the place from which they may be obtained;

d) The place and deadline for the submission of bids, and

e) The announcement which shows place and time for opening of bids and that bidders or representatives may present.

፳፱ የጨረታ ሰነድ

በተጫራቾች መካከል የሚደረገው ውድድር በተሟላ፣ ገለልተኛና ተጨባጭ መሠረት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ለማድረግ የጨረታው ሰነድ በቢሮዉ የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ መሠረት በማድረግ በቂ መረጃ በያዘ መልኩ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡ በተለይም ሰነዱ የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል፡-

ሀ/ የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀትና ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን፣

ለ/ የመጫረቻ ሰነዱን ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀን፣ የመጫረቻ ሰነዱ የሚላክበትን አድራሻ፣ ጨረታው የሚከፈትበትን ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ፣ እንዲሁም የተጫራቾች ወኪሎች በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ ሊገኙ የሚችሉ መሆኑን የሚገልፅ መረጃ፣

ሐ/ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረቢያ ቅፆች፣ እንዲሁም አግባብነት እስካለው ድረስ የጨረታ ማስከበሪያ ቅፆች፣

መ/ ከዋናው የመጫረቻ ሰነድ ጋር መቅረብ ያለባቸውን ተጨማሪ ኮፒዎች፣

ሠ/ የውሉን አጠቃላይ እና ልዩ ሁኔታዎች፣

ረ/ እንደአግባብነቱ ዕቃውን ለማቅረብ ወይም ሥራውን ለማጠናቀቅ ይወስዳል ተብሎ የሚገመተውን የጊዜ ገደብ ጨምሮ ተፈላጊውን የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር፣

ሰ/ ተጫራቹ በጨረታው ለመሳተፍ ብቃት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያቀርባቸውን መረጃዎች ዓይነት እንዲሁም የፋይናንስ አቋሙን እና ሕጋዊነቱን ለማረጋገጥ ማቅረብ ያለበትን መረጃ፣

ሸ/ ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣

ቀ/ ጨረታውን ለመገምገም እና በጨረታው አሸናፊ የሆነውን ለማስታወቅ የሚያገለግሉ መስፈርቶችን እና ለእያንዳንዱ መስፈርት የተሰጠውን ነጥብ፣

በ/ ግዥውን የሚፈፅመው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የጨረታው አሸናፊ ይፋ ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሠረዝ መብት ያለው መሆኑን፣

ተ/ የቢሮዉ ሀላፊ በሚያወጣው መመሪያ በልዩ ሁኔታ ለተፈቀዱ ግዥዎች በኮንትራት አፈጻፀም ወቅት የዋጋ ማስተካከያ ሊደረግ የሚችል ስለመሆኑ እና የዋጋ ማስተካከያው የሚደረግበትን ሁኔታ እና አፈጻፀሙን

29. ***Bidding Documents***

The bidding documents shall contain sufficient information to enable competition among the bidders to take place on the basis of complete, neutral and objective terms. In particular, bidding documents must include;

a) Instructions for the preparation and submission of bids;

b) information about the final date for receipt of bids, the address to which bids must be sent the date, hour and place of opening as well as an announcement that bidders of their representatives are allowed to attend the opening ceremony;

c) bid submission forms and where applicable, forms of bid security to be provided;

d) the number of copies to be submitted with the original bid;

e) the general and specific conditions of the contract,

f) specification of requirements, including time limit for delivery or completion of the task, as appropriate;

g) evidence to be provided by the bidder to demonstrate its qualifications as well as its fiscal and legal standing,

h) the period during which the bid remains in force;

i) the criteria and the points given to each criterion for evaluation of bids and award of the contract;

j) a reservation to the effect that the public body may reject all bids at any time prior to the notification of award, and

k) the price adjustment that may be made during contract implementation and the conditions and the manner under which such price adjustments prescribed by the Head of Bureau.

**፴ የጨረታ ሰነድ ሽያጭ**

፩. የጨረታ ሰነድ የመሸጫ ዋጋ ለጨረታው ሰነድ ዝግጅት እና ሰነዱን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ለማቅረብ ከወጣው ወጪ ባልበለጠ መተመን ይኖርበታል።

፪. የጨረታ ሰነዱ ጨረታው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ጨረታው እስከሚዘጋበት ጊዜ ድረስ ባሉት የስራ ቀናት እና በጨረታ ማስታወቂያው በተገለፀው አኳኋን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርስ መደረግ አለበት፡

፫. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ አግባብ ሆኖ ሲያገኘው የጨረታ ሰነዱ በነፃ እንዲሰጥ ሊፈቅድ ይችላል።

**፴፩. <u>በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ</u>**

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በራሳቸው ወይም የጨረታ ሰነድ ከገዙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መነሻ የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የጨረታ ሰነዶችን ይዘት ለማሻሻል ይችላሉ።

፪. የተደረገው ማሻሻያ በፅሑፍ ተዘጋጅቶ የጨረታ ሰነዶችን ለገዙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሁሉ በተመሳሳይ ጊዜ መላክ አለበት።

፫. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የጨረታ ሰነዱን ይዘት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ያገኘው እና በማሻሻያው የተመለከቱ ማስተካከያዎችን ለማድረግ በቂ ጊዜ የሌለ መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማሻሻያውን መሠረት አድ ርገው የጨረታ ሰነዱን ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው ለማድረግ የግዥውን ባህርይ መሠረት በማድረግ የጨረታ ውን ማቅረቢያ ጊዜ ለተወሰኑ ቀናት ሊያራዝም ይችላል ።

***30. Provision of Bidding Documents***

1. Bid documents shall be made available to candidates at a price not exceeding the cost of reproduction and delivery of such documents to candidates.
2. The bidding document shall be delivered to candidates on working days between the date of publication of the invitation to bid and the closing date of the bid and in the manner specified in the invitation to bid.
3. Where it deems it to be appropriate, the public body may make the bidding document available to candidates free of charge.

***31. Modifications to Bidding Documents***

1. At any time prior to the deadline for submission of bids, the public body may, on its own initiative or in response to an inquiry by a candidate having purchased the bidding documents, modify the bidding documents by issuing an addendum, which becomes an integral part of the bidding documents.
2. Any addendum shall be communicated promptly to all candidates having purchased the bid documents at the same time.
3. if the public body considers it necessary to amend the bidding document and if it determines that there is no enough time to incorporate the modification, it may postpone the closing date by a number of days, depending on the procurement object, which is sufficient to enable the bidders object, which is sufficient to enable the bidders to take the addendum to account in preparing their bids.

## ፴፪ የጨረታ ማስከበሪያ

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ ተጫራቾች ከመጫረቻ ሰነዶቻቸው ጋር የጨረታ ማስከበሪያ የማቅረብ ግዴታ እንዳለባቸው መግለፅ አለባቸው፡፡ የጨረታ ማስከበሪያው መጠን በጨረታው ኃላፊነት በተሞላው ሁኔታ የማይሳተፉትን ለማስቀረት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡

፪. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ የተገለፀው ቢኖርም የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ የሚያስፈልግባቸው የግዥ አይነቶች እና የጨረታ ማስከበሪያው መጠን የቢሮዉ ሀላፊ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፫. የጨረታ ማስከበሪያው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ራሱን ከውድድሩ ካገለለ ወይም አሸናፊውን ተጫራች በሚመለከት አሸናፊነቱ ከተገለፀለት በኋላ ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ሆኖ ካልተገኘ ወይም እንዲያቀርብ የተጠየቀውን የውል ማስከበሪያ ካላቀረበ የጨረታ ማስከበሪያው ውርስ ይደረጋል፡፡

## ፴፫. <u>የመጫረቻ ሰነድ ስለማቅረብና ስለመቀበል</u>

፩. የመጫረቻ ሰነድ በፅሑፍ ተዘጋጅቶና ተፈርሞበት በታሸገ ኤንቨሎፕ ውስጥ ሆኖ በጨረታ ማስታወቂያው ከተመለከተው የጊዜ ገደብ በፊት በተገለፀው ቦታ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

፪. የመጫረቻ ሰነዱ ትልቅ በመሆኑ በጨረታ ሣጥን ውስጥ ሊቀመጥ የማይችል ከሆነ የመጫረቻ ሰነዱን የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የግዥ ስራ ክፍል ተረክቦ ገቢ የተደረገበትን ቀንና ሰዓት የሚያሳይ ማረጋገጫ ሰዕጨ ተወዳዳሪው መስጠት አለበት፡፡

፫ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የመጫረቻ ሰነዱን ለማቅረቢያ ከተወሰነው ጊዜ በኋላ የቀረበ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

## ፴፬. <u>ጨረታን ስለመክፈት</u>

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በጨረታ ሰነዱ የተመለከተው የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው የጊዜ ገደብ

## 32. *Bid Security*

1. Public bodies shall include in the bidding documents a condition that bids must be accompanied by a bid security. The amount of such bid security shall be sufficient to discourage irresponsible bidders.
2. Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, procurement in respect of which bid security is required and the amount of bid security thereof, is to be prescribed by the directive to be issued by the Head of Bureau.
3. A bid security will be forfeited if a bidder withdraws his bid within the validity period thereof or in the case of a successful bidder, if the bidder repudiates the contract or fails to famish performance security, if so required

## 33. *Submission and Receipt of Bids*

1. Bids shall be submitted in writing signed and in a sealed envelope, to the place and before the deadline stated in the invitation to bid.
2. The public body shall give a receipt to the bidder indicating the time and date on which the bid document was submitted, where it becomes impossible to put the bid document in a bid box due to its large size.
3. Without prejudice to the provisions of sub-article (2) of this Article, a bid document submitted after the deadline for submission shall not be accepted.

## 34. *Opening of Bids*

1. At the time stipulated in the bidding document for opening of bids, which should follow immediately after the deadline for submission

እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ የመጫረቻ ሰነድ ከማቅረቢያ የጊዜ ገደብ በፊት የቀረቡ የመጫረቻ ሰነዶችን መክፈት አለበት፡፡

፪ የተጫራቹ ስም እና በእያንዳንዱ የመጫረቻ ሰነድ የቀረበው የመጫረቻ ዋጋ ፣ የተሰጠ ቅናሽ እና የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እንደ ግኘው ሁኔታ ተጫራቾች አንፃራዊ ደረጃቸውን ለማወቅ ይረዳቸዋል ብሎ የሚያምንባቸው ሌሎች መረጃዎች ከፍ ባለ ድምፅ መነበብ እና መመዝገብ እንዲሁም ተጫራቾች በጠየቁ ጊዜ የተመዘገበውን ዝርዝር እንዲያገኙ መደረግ አለበት፡፡

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው ቢኖርም የቴክኒክና የፋይንናስ መወዳደሪያ ሀሳብ በሁለት ፖስታ የቀረበ በሚሆንበት ጊዜ የመጫረቻ ዋጋው የሚነበበው የቴክኒክ ግምገማው ከተጠናቀቀ በኋላ ይሆናል፡፡

## ፴፭. <u>የመጫረቻ ሰነዶችን ስለመመርመር እና ስለመገምገም</u>

፩. ጨረታውን ለመመርመርና ግምገማውን ለማከናወን የሚረዳ ሆኖ ሲገኝ፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ተጫራቾች ባቀረቡት የመጫረቻ ሰነድ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ሆኖም የዋጋ ለውጥን ጨምሮ የመጫረቻ ሰነዱ ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትል ሀሳብ ማቅረብ ወይም መፍቀድ አይቻልም፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ቢኖርም የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በጨረታ ምርመራው ወቅት የተገኙ የሂሳብ ስህተቶችን ለማረም ይችላል፡፡ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እነዚህን ማስተካከያዎች የመጫረቻ ሰነዱን ላቀረበው ተጫራች በአፋጣኝ መግለፅ አለበት፡፡

፫. በጨረታው ሰነድ ከተዘረዘሩት ባህሪያት፣ የውል ቃሎች፣ ሁኔታዎች እና ሌሎችም ተፈላጊ ነጥቦች ጋር በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ቢኖረውም መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታው ቁምነገር ሳይለወጥ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ስህተት ወይም ግድፈት ቢኖረውም የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ጨረታውን እንደተሟላ አድርጐ ሊቀበል ይችላል፡፡ ማናቸውም ልዩነት እስከተቻለ ድረስ በአሀዝ ተገልፆ በጨረታ ግምገማ እና ውድድር ወቅት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

of bids, the public body shall open all bids received before the deadline

2. The name of the bidder and the total amount of each bid, discounts offered and any such information as the public body deems necessary to let the bidders know their relative rank shall be read out aloud and recorded and a copy of the record shall be made available to any bidder on request.
3. Notwithstanding the provisions of sub-article (2) of this Article, the envelope containing the price offered by the bidder shall be read after the evaluation of the technical proposal where technical and financial proposals are submitted in two separate envelops.

## *35. Examination and Evaluation of Bids*

1. The public body may ask bidders for clarification of their bids in order to assist in the examination and evaluation of bids; however, no change in the substance of the bid, including changes in price, shall be sought, offered or permitted.
2. Notwithstanding sub-Article (1) of this article, the public body shall correct arithmetical errors that are discovered during the examination of bids. The public body shall give prompt notice of any such correction to the bidder that submitted the bid.
3. The public body may regard a bid as responsive even if it contains minor deviations that do not materially alter or depart from the characteristics, terms, conditions and other requirement set forth in bidding documents or if it contains errors or oversights that are capable of being corrected without touching on the substance of the bid. Any such deviations shall be take in to consideration to the extent as it is possible in case of examination and competition of bids.

፬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ጨረታው የተሟላ ነው ብሎ ሊቀጥል የሚችለው በጨረታው ሰነድ የተመለከቱትን ተፈላጊ ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው ነው፡፡

፭. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የማያሟሉ ተጫራቾችን አሸናፊ አድርጎ መምረጥ የለበትም፡፡

ሀ/ ተጫራቹ በአንቀጽ ፲፱(፩) የተጠቀሱትን መስፈርቶች ማሟላት የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣

ለ/ ተጫራቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የተደረገውን የሂሣብ ማስተካከያ የማይቀበል ሆኖ ሲገኝ፣

ሐ/ የቀረበው የመጫረቻ ሰነድ በጨረታ ሰነዱ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ፣

፮ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፰ በተደነገገው መሠረት አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ በጨረታ ሰነዱ በተመለከተው የግምገማ መስፈርት መሠረት ተፈላጊውን ያሟሉ የመጫረቻ ሰነዶችን መገምገምና ማወዳደር አለበት፡፡ በጨረታ ሰነድ ያልተመለከተ የማወዳደሪያ መስፈርት በጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፡፡

፯ ማናቸውም ተጫራች በመጫረቻ ሰነዱ ከተመለከተው ውጪ በጨረታው አሸናፊ ለመሆን ያቀረበውን የመጫረቻ ዋጋ እንዲለውጥ ወይም ያቀረበውን የመወዳደሪያ ሐሳብ እንዲያሻሽል ወይም ይህንን ለመፈፀም ግዴታ እንዲገባ ሊጠየቅ ወይም ሊገደድ አይችልም፡፡

፰ በጨረታ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው፣

ሀ/ በጨረታ ግምገማ የቴክኒክ መመዘኛዎችን ማሟላቱ የተረጋገጠ እና አነስተኛ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች፣ ወይም

4. Without prejudice to sub-article (3) of this Article, the public body may regard a bid as responsive only if it conforms to salient requirements set forth in the bidding documents.
5. Any public body shall not award a contract when.
   a. the bidder has failed to demonstrate, in the manner provided in Article 19(1) of this proclamation, that it is qualified;
   b. the bidder does not accept a correction of an arithmetical error made pursuant to sub-article (2) of this Article;
   c. the bid submitted is found not meeting the conditions specified in the bid document.
6. In the process of selection the successful bidder, the public body shall only consider substantially responsive bids for further evaluation and comparison, as defined in sub-article (8) of this Article in accordance with the criteria setforth in the bidding documents. No criterion shall be used that has not been set forth in the bidding documents.
7. No bidder may be required to change the price offered in his bid or otherwise modify his proposal or to assume obligation to do so except as set forth in the bidding document.
8. The successful bid shall be:
   a. the bid that is found to be responsive to the technical requirements and with the lowest evaluated price;

ለ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በጨረታው ሰነድ ውስጥ አሸናፊው ተጫራች የሚመረጥበትን መስፈርት የገለፀ ከሆነ፣ በጨረታ ሰነዱ የሠፈረውን የጨረታውን ኢኮኖሚያዊ እሴት የሚወስነውን መስፈርት መሠረት በማድረግ በሚካሄድ ግምገማ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው የጨረታ ሐሳብ ያቀረበው ተጫራች አሸናፊ ይሆናል:: ሆኖም መስፈርቱ በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ፣ በአኃዝ ሊገለፅ የሚችል ሆኖ በግምገማው ሂደት አንፃራዊ ክብደት የሚሰጠው እና እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ የሚገለፅ መሆን አለበት::

ሐ/ ቢሮዉ በሚያወጣው ዝርዝር መመሪያ በሚወሰነው መሰረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፰ በፊደል (ሀ) ወይም (ለ) መሰረት የተመረጠው ተጫራች ህጋዊነት፣ የፋይናንስ እና የቴክኒክ አቅም በመጫረቻ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሰረት መሆኑ በድሕረ ግምገማ ሲረጋገጥ፣

፱. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የግምገማውን ውጤት በአጭሩ የሚገልፅ የግምገማ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት::

**፴፮. <u>በሚስጥር ስለሚያዙ አሠራሮች</u>**

ጨረታው ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ከጨረታ ምርመራ፣ ከማብራሪያ፣ ከግምገማ እና አሸናፊውን ተጫራች በሚመለከት ከቀረበው የውሣኔ ሀሳብ ጋር የተያያዙ መረጃዎች በሚስጢርነት መጠበቅ ያለባቸው ሲሆን፣ አሸናፊው ተጫራች እስከሚገለፅ ድረስ ለተጫራቾች ወይም ከሥራው ሂደት ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ሰዎች መገለፅ የለባቸውም::

**፴፯ <u>ከአሸናፊ ተጫራች ጋር ድርድር ስለሚደረግባቸው ጉዳዮች</u>**

ሀ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር የጨረታ ሰነዱ ላይ ባልተጠቀሱ የውል አፈፃፀም ጉዳዮች ላይ ድርድር ሊያደርግ ይችላል::

ለ/ በአንቀፅ ፵፫ ላይ በተጠቀሰው መሰረት ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ለሚፈፀም ግዥ ካልሆነ በስተቀር አሸናፊው ተጫራች ባቀረበው ዋጋ እና ከዋጋ ጋር ግንኙነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ድርድር ማድረግ አይችልም::

b. if the public body has so stipulated in the bidding documents, the bid offering better economic advantage ascertained on the basis of factors affecting the economic value of the bid which have been specified in the bidding documents, which factors shall, to the extent practicable, be objective and quantifiable, and shall be given a relative weight in the evaluation procedure or be expressed in monetary terms wherever practicable;

c. where it is ascertained by post bid evaluation, in accordance with the specific directive to be issued by the Bureau, that the legal, financial and technical standing of the candidate selected as the successful bidder in accordance with sub-article (a) or (b) of this Article conforms to the requirements stated in the bidding document.

9. The public body shall prepare an evaluation report, containing a summary of the examination and evaluation of bids,

***36. Process to be Confidential***

After the opening of bids, information relating to the examination, clarification, and evaluation of bids and recommendations for award must not be disclosed to bidders or other persons not officially concerned with this process until the award of the contract is announced.

***37. Matters Subject for Negotiation with the Successful Bidder***

1. The public body may negotiate with the successful bidder on matters of contract performance not dealt within the bidding document.
2. Except in a single source procurement provided for in Article 43 of this proclamation the public body may not negotiate on the price offered by the successful bidder and on other issues related to price.

## ፴፰. አሸናፊነትን ስለመግለፅና ውል ስለመፈራረም

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከተጫራቹ የቀረበው የመጫረቻ ሰነድ ፀንቶ የሚቆይበት ቀን ከማለፉ በፊት በጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች አሸናፊነቱን መግለፅ አለባቸው:: የአሸናፊነት መግለጫ ማስታወቂያው ውሉ የሚፈረምበትን ቀን የሚገልፅ ይሆናል:: በጨረታው ተሸናፊ ለሆኑ ተጫራቾችም የአሸናፊውን ስም እና የተሸነፉበትን ምክንያት የሚገልፅ ማስታወቂያ በደብዳቤ ሊደርሳቸው ይገባል::

፪. በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና በአቅራቢው መካከል ውል ተመስርቷል የሚባለው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተደረሰባቸውን ጉዳዮች በሙሉ የሚይዘው የውል ሰነድ ሲፈረም ይሆናል::

፫. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ለተሸናፊዎቹ ተጫራቾች ተሸናፊነታቸውን የሚገልፀው ማስታወቂያ ከመድረሱ እና ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ ላይ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የግዥውን ውል መፈረም የለበትም::

፬. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የውል አስተዳደርን በሚመለከት ሊከተል የሚገባው አሠራር ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

## ፴፱ የውል ማስከበሪያ

አቅራቢው በውሉ መሠረት ባለመፈፀሙ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ማካካሻ የሚውል የውል ማስከበሪያ ለባለበጀት መ/ቤቱ መስጠት አለበት:: የውል ማስከበሪያ የሚጠየቅባቸው የግዥ ዓይነቶች፣ የውል ማስከበሪያው ዓይነትና መጠን ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

## ፵. የቅድሚያ ክፍያ

፩. በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም ለአቅራቢው የሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ መጠን እና አፈፃፀም ቢሮዉ በሚወጣ መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል::

፪. የቅድሚያ ክፍያ ሊፈፀም የሚችለው አቅራቢው በቅድሚያ ክፍያ መልክ ከሚወስደው ገንዘብ መጠን ጋር እኩል የሆነ ዋስትና ሲያቀርብ ይሆናል::

## 38. *Notification of Award and Signing of Contract*

1. Prior to the expiry of the period of bid validity, the public body shall notify the successful bidder that its bid has been accepted. The notification of award shall specify the time within which the contract must be signed. The unsuccessful bidders shall also be informed as to who the successful bidder is and why they have lost the bid.

2. The existence of a contract shall be confirmed through the signature of a contract document incorporating all agreement between the parties.

3. The contract shall not be signed by the public body prior to the receipt of the notice by the unsuccessful bidder and before the period specified in the directive to be issued by the Bureau has lapsed.

4. The procedures that public body has to follow in administering the contract shall be prescribed by a directive to be issued by the Bureau.

## 39. *Contract Security*

A supplier shall provide the public body with a contract security to make good any damage the public body may sustain as a result of default by the supplier under the contract. The type of procurement for which contract security is required and the type and amount of contract security shall be determined by a directive to be issued by the Bureau.

## 40. *Advance Payment*

1. The amount of advance payment that may be allowed to suppliers in public procurement and the manner in which it is made available shall be determined by the directive to be issued by the Bureau.

2. Advance payment may be effected only where a supplier furnishes advance payment guarantee in an amount equal to the advance payment.

## ምዕራፍ አምስት
## ውስን ጨረታ

**፵፩. በውስን ጨረታ ለመጠቀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች**

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በውስን ጨረታ ግዥ መፈፀም የሚችሉት የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው።

፩/ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ወይም

፪/ የግዥው መጠን ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ሲሆን ፣

፫/ ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ የሚገለፅ ሆኖ በተደጋጋሚ ጨረታ ወጥቶ ተወዳዳሪ ያልተገኘ ሲሆን፣

**፵፪. የውስን ጨረታ አፈፃፀም**

የውስን ጨረታ ሥርዓቶች ከግልፅ ጨረታ ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ፣ የውስን ጨረታ የሚከተሉትን ልዩ አሠራሮች ይከተላል።

፩. በአንቀፅ ፵(፩) መሠረት ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ ሲሆን የጨረታው ጥሪ ለነዚሁ አቅራቢዎች በሙሉ ይላካል።

፪. የውስን ጨረታው የሚካሔደው በአንቀፅ ፵(፪) ወይም (፫) ላይ በተጠቀሰው ምክንያት ከሆነ የጨረታ ጥሪው እስከተቻለ ድረስ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት አቅራቢዎች መካከል የሚከተለውን መሠረት በማድረግ ይፈፀማል።

ሀ/ አመራረጡ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ለተመዘገቡት ፍትሐዊ የሆነ ዕድል የሚያስገኝ መሆን ይኖርበታል።

ለ/ ጥሪ የሚደረግላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ብዛት ውጤታማ ውድድር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ሲሆን፣ እስከተቻለ ድረስ የተወዳዳሪዎች ቁጥር ከ ፭ ማነስ የለበትም።

፫. ለመጫረቻ ሰነድ ዝግጅት የሚፈቀደው ጊዜ ለዚህ የግዥ ዘዴ በግዥ መመሪያው ከተወሰነው አነስተኛው የቀን ብዛት ያነሰ ሊሆን አይችልም። ሆኖም ለጨረታው ጥሪ የተደረገላቸው

## CHAPTER FIVE
## RESTRICTED TENDERING

**41. *Conditions for use of Restricted Tendering***

Public bodies may use restricted tendering as a method of procurement only where the following conditions are satisfied:

1. it is a ascertained that the required object of procurement is available only with limited suppliers;
2. the cost of procurement does not exceed the amount of cost that the Bureau will issue
3. where a repeated advertisement of the invitation to bid fails to attract bidders in respect of a procurement subject to the directive to be issued by the Bureau.

**42. *Procedure for Restricted Tendering***

Restricted tendering procedures are the same as those applied in open tendering, except that:

1. where the object of procurement is available only with limited suppliers in accordance with Article 40(1) of this proclamation the invitation to bid shall be sent to all such suppliers;
2. if restricted tendering is used for the reason stated in Article 40 sub-articles(2) or (3) of this proclamation, the invitation to bid shall, as far as possible, be sent to limited suppliers chosen form among those registered in the supplies list on the basis of the following consideration.
   a. any selection shall allow opportunities for suppliers on the list,
   b. the number of suppliers to whom the invitation to bid is sent shall be such that it is sufficient to ensure effective competition and shall not as far as possible be less than five competators
3. the time allowed for preparation of bids shall not be less than the minimum number of days stated in the procurement directive for this method of

ተጫራቾች በሙሉ የመጫረቻ ሰነዳቸውን ከጨረታው መዝጊያ ቀን በፊት ካስገቡ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ለተጫራቾች በቂ የቅድሚያ ማስታወቂያ በመስጠት ጨረታውን በጨረታ ማስታወቂያው ላይ ከተቀመጠው ቀን አስቀድሞ ሊከፍት ይችላል፡፡

፬. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በውስን ጨረታ ግዥ የሚፈፅመው በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፵፩ (፩) ላይ በተገለፀው ምክንያት ሲሆን የጨረታ ማስከበሪያ ማቅረብ የሚያስፈልግ መሆን ያለመሆኑን ይወስናል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት
## ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ

### ፵፫. ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈፀም የሚችሉት የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው፡፡

ሀ/ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ/ ለዕቃዎች፣ ወይም ለተገጣሚዎች ተጨማሪ መለዋወጫ ዕቃዎችን ወይም ተጨማሪ አገልግሎቶችን ከመጀመሪያው አቅራቢ መግዛት ሲፈለግ፣ ወይም ከሌላ አቅራቢ ግዥው ቢፈፀም የሚገዛው ተገጣሚ መሣሪያ ወይም አገልግሎት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከሚጠቀምበት መሣሪያ ወይም አገልግሎት ጋር የማይጣጣም ሆኖ በመገኘቱ ከመጀመሪያ አቅራቢ መለዋወጫዎችን፣ አገልግሎቶችን ወይም ተገጣሚዎችን መግዛት አስፈላጊ ሲሆን፣

ሐ/ በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ያልታሰቡ ሁኔታዎች በማጋጠማቸው ምክንያት በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ማሠራት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እና የቴክኒክ ወይም በኢኮኖሚ ምክንያቶች እነዚህን ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች ከመጀመሪያው ውል ነጥሎ ማሠራት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ፣

Procurement However, if all suppliers invited to participate in the bid have submitted their bids before the closing date, the public body may open the bid ahead of schedule by giving bidders prior notice;

4. if the public body uses restricted tendering for the reason stated on article 41(1) of this proclamation, it shall determine whether it is necessary to require the candidates to submit bid security.

## CHAPTER SIX
## DIRECT PROCUREMENT

### 43. Conditions for use of Direct Procurement

1. Public bodies may use direct procurement only where the following conditions are satisfied:
   a. when in absence of competitions for technical reasons the goods, works consultancy or other required services can be supplied or provided only by one candidate;
   b. for additional deliveries of goods by the original supplier which are intended either as parts of replacement for exaction supplies, services or installations or as he extension of existing supplies, services or installation where a change of supplies would compel the public body to procure equipment or services not meeting requirements of interchangeability with already existing equipment or services;
   c. within limits defined in the procurement directive, when additional works, which have been not included in the initial contract have, through unforeseeable circumstances, become necessary since the separation of the additional works from the initial contract would be difficult for technical or economic reasons;

መ/ በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አሸናፊው ከተመረጠ በኋላ በተፈረመ ውል የመጀመሪያው ግዥ የተከናወነባቸው ዓይነት ተመሳሳይ ሥራዎች ወይም አቅርቦቶች በድጋሚ እንዲሠሩ ወይም እንዲቀርቡ ማድረግ በማስፈለጉ ተጨማሪ ውል መፈፀም አስፈላጊ ሲሆን፣

ሠ/ በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመጀመሪያው የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ውል አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ መጠናቀቁ እና ውሉ እንዲራዘም ማድረግ ቁጠባንና ቅልጥፍናን የሚያስገኝ መሆኑ በመረጋገጡ አገልግሎቱን መቀበል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

ረ/ በጣም አስቸኳይ ከመሆኑ የተነሳ ከባድ ችግር የሚፈጥርና በመ/ቤቱ ሥራ አፈፃፀም ላይ ጉዳትን የሚያስከትል በመሆኑ ምክንያት በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የተፈቀደ ግዥ፣

ሰ/ ዝርዝር አፈፃፀሙ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የመንግስት መ/ቤቶች ለሚኖራቸው የተለየ የግዥ ፍላጎት ማሟያ ከገበያ በለቀማ ግዥ መፈፀም የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ፣

ሸ/ ለአጭር ጊዜ የሚቆይ እና ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ልዩ ጥቅም በሚያስገኝ ሁኔታ የሚፈፀም የዕቃ ግዥ ሲሆን ነው:: ይህ ንዑስ አንቀጽ የሚያገለግለው በመደበኛ አቅራቢነት ያልተሠማሩ ሰዎች ለሚሸጡዋቸው ዕቃዎች ሲሆን፣ በመደበኛ አቅራቢነት ከተሠማሩ አቅራቢዎች አዘውትረው የሚፈፀሙ ግዥዎችን አይጨምርም::

d. within limits defined in the procurement directives. for new works consisting of the repetition of similar works which conform to a basic project of which an initial contract has been awarded on the basis of open or restricted bidding;

e. within limits defined in the procurement directives. for continuation of consultant services, where the original contract has been satisfactorily performed and the continuation is likely to lead to gains in

f. the head of the public body has determined that the need is one of pressing emergency in which delay would create serious problems and therefore injurious to the performance of that public body;

g. where situations arise in which shopping becomes necessary to meet the special procurement needs of public bodies. The manner of implementation of this provision shall be prescribed by the directive to be issued by the Bureau

h. For purchase of goods made under exceptionally advantageous conditions which only arise in the very short term. This provision is intended to cover unusual disposals by firms, which are not normally suppliers. It is not intended to cover routine purchases form regular suppliers.

፪ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በግዥ መመሪያው ከሚወሰን የገንዘብ መጠን ያልበለጡ ጥቃቅን ግዥዎችን ከአንድ አቅራቢ በሚፈፀም የግዥ ዘዴ በመጠቀም መግዛት ይችላሉ፡፡

፫. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ (ሰ) እና ፪ መሰረት ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ለሚፈፀሙ ግዥዎች ውል መዋዋል አስፈላጊ አይሆንም፡፡

፬. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ይህ የግዥ ዘዴ በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ውድድር እንዳይኖር ወይም በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ለመፍጠር ታስቦ ጥቅም ላይ ያልዋለ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፵፬. <u>ከአንድ አቅራቢ የሚከናወን ግዥ አፈፃፀም</u>

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፵፫(፩) በተደነገገው መሠረት ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈፀም ሲፈልጉ ግዥውን መፈፀም ያስፈለገበትን ምክንያት እና የሚገዛውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራት፣ ብዛት፣ የማቅረቢያ ጊዜና ሁኔታዎች የሚያብራራ መግለጫ ማዘጋጀትና ዋጋን ጨምሮ ከአቅራቢው ጋር በግልፅ መደራደር አለባቸው፡፡ በአንቀፅ ፵፪ ንዑስ አንቀፅ ፫ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርድሩ ከተካሄደ በኋላ ግዥ ለመፈፀም የሚደረሰው ስምምነት በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በሚፈረም ውል መረጋገጥ አለበት፡፡

፪. ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ለሚፈፀም ግዥ ድርድር የማድረጊያ አትኩሮተ-ነጥቦች ዝርዝር በመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ፀድቆ ለተደራዳሪዎች ሊሰጥ ይገባል፡፡

## ምዕራፍ ሰባት
## <u>በመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ</u>

፵፭ <u>በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች</u>

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ግዥ መፈፀም የሚችሉት ለምክር አገልግሎት ወይም ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ውስጥ የምክር አገልግሎቱ ዋጋ ከ፶ በመቶ በላይ ለሚሆን ግዥ ነው፡፡

2. Public bodies may use direct procurement when the cont act price does not exceed an amount stated in the procurement directive.

3. It shall not be necessary to conclude a contract in respect of direct procurements effected in accordance with sub-articles (1) (g) and (2) of this Article;

4. Public bodies shall ensure that this method is not resorted to with a view to avoiding possible competition or in a manner which would constitute a means of discrimination among candidates.

**44. *Procedure for Direct procurement***

1. When the public body engages in direct procurement according to Article 43(1) of this proclamation, it shall prepare a description of its needs and any special requirements as to quality, quantity, terms and time of delivery, and shall be free to negotiate on price and conditions of offer with the sole candidate. Without prejudice to the provisos of sub-article (3) of Article 42 of this proclamation, any agreement reached to conduct the Direct Procurement.
2. The salient points to focus on in the negotiation of contracts for direct procurements shall be approved by the head of the public body concerned and communicated to the negotiators.

## CHAPTER SEVEN
## REQ''EST FOR PROPOSALS

**45. *Conditions for use of Request for Proposal***

Public bodies may engage in procurement by means of request for proposals when it seeks to obtain consultancy services or contracts for which the component of consultancy services represents more than 50% of the amount of the contract.

**፵፮ በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የሚከናወን ግዥ አፈፃፀም**

፩. የምክር አገልግሎቱ የሚጠይቀው ወጪ በመመሪያ ከሚወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ ከሆነ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚመረጡት በውድድሩ ተሳታፊ ለመሆን የሚፈልጉ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ በማስታወቂያ ከተጋበዙ በኋላ ይሆናል፡፡

፪. የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ከሦስት ላላነሱ እና ከሰባት ላልበለጡ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ለሚመረጡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች መላክ ይኖርበታል፡፡

፫. የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፤

ሀ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ስምና አድራሻ፤

ለ/ የሚፈለገውን አገልግሎት የሚያሳይ የማጣቀሻ ፅሑፍ፤

ሐ/ የጥቅም ግጭትን ሊያስከትል የሚችል የምክር አገልግሎት በሚሆንበት ጊዜ ለዚህ ዓይነቱ ውድድር የሚቀርቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከምክር አገልግሎቱ በማስከተል ከምክር አገልግሎቱ ጋር በተያያዘ ከሚከናወኑ የዕቃ አቅርቦትና የግንባታ ሥራዎች ራሳቸውን ማግለል የሚገባቸው መሆኑን የሚገልፅ ማሳሰቢያ፤

መ/ የመወዳደሪያ ሀሳቦችን መገምገሚያ መስፈርቶችን፤ ለዋጋና ለሌሎች መስፈርቶች የሚሰጠውን ነጥብ፤ መስፈርቶቹ የመወዳደሪያ ሀሳብ በሚገመገምበት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉበትን አኳኋን፤

ሠ/ የመወዳደሪያ ሀሳብ የሚቀርብበትን ቦታና የመጨረሻ ቀን፤

፬. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመወዳደሪያ ሀሳብ ለማዘጋጀት የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው የሚገባ ሲሆን፤ የጊዜ ገደቡ በግዥ መመሪያ ይወሰናል፡፡

፭. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ አንደኛ ሆኖ ከተመረጠው ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር በመወዳደሪያ ሀሳቡ ውስጥ የተመለከተውን የአገልግሎቱን ባህሪ፣ መጠን እና አደረጃጀት የሚመለከት ድርድር ማድረግ ይችላል፡፡

**46. *Procedure for Request for Proposals***

1. The selection of candidates for consultancy services above a threshold to be determined by a directive shall be made after inviting candidates to submit expression of interest.
2. Requests for proposals shall be addressed to not less than three and not more than seven candidates selected by the public body.
3. A request for proposals shall contain at lease the following information.
   a. the name and address of the public body;
   b. description of the services required, normally through terms of reference;
   c. in the case of consultancy assignments which may involve potential conflicts of interest, a reminder that candidates for such assignments must exclude themselves from procurement of goods and works which may follow as a result of or in connection with the consultancy agreement;
   d. the criteria for evaluating the proposals the relative weight to be given to price and other criteria, and the manner in which they will be applied in the evaluation of proposals;
   e. place and deadline for the submission of proposals.
4. Candidates shall be given adequate time in which to prepare their proposals; such time frame shall be determined by the procurement directive.
5. The public body may negotiate with the first ranked candidate with respect to the nature, volume and organization of the services included in their proposals.

፮ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል በአሸናፊነት ሊመርጥ የሚችለው በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ሰነድ በተመለከተው የመገምገሚያ መስፈርት መሠረት በሚካሔደው ግምገማ ያቀረበው የመወዳደሪያ ሀሳብ ይበልጥ ጠቃሚ ሆኖ የተገኘውን ዕጩ ተወዳዳሪ ነው።

## ምዕራፍ ስምንት

## በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ

### ፵፯. በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት ግዥው ቢሮዉ በሚያወጣው የግዥ መመሪያ ከሚወስነው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ እና የሚገዙትም ለገበያ የተዘጋጁ ዕቃዎች ወይም የታወቀ ገበያ ያላቸው የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች፤ የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ሲሆኑ ነው፡

### ፵፰. በዋጋ ማቅረቢያ የሚካሔድ ግዥ አፈፃፀም

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚቻል እስከሆነ ድረስ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡ አቅራቢዎች መካከል ቢያንስ ሦስት አቅራቢዎችን የዋጋ ማቅረቢያ እንዲሰጡ ሊጠይቁ ይገባል።

፪ በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም አንድ አይነት ግዥ አማራጭ አቅራቢዎች እስካሉ ድረስ በተደጋጋሚ የተወሰኑ አቅራቢዎችን ብቻ በመጋበዝ ማወዳደር አይቻልም። በመሆኑም የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እስከተቻለ ድረስ በዘርፉ ለተሰማሩ ሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተመጣጣኝ የመወዳደር ዕድል መስጠቱን ማረጋገጥ አለበት።

፫. በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚላከው መጠየቂያ የሚቀርበውን ዕቃ ወይም፣ የግንባታ ስራ ፣ ወይም የምክር ወይም ሌላ አገልግሎት ጥራት፣ ብዛት፣ የማቅረቢያ የውል ቃሎች እና ጊዜ እንዲሁም ሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ፍላጐቶች ዝርዝር የሚገልፅ መሆን አለበት።

፬. ግዥ የሚፈፅመው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ለማዘጋጀት የሚያስችል በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል።

6. Any award by the public body shall be made to the candidate whose proposal is most advantageous, determined in accordance with the criteria and procedures for evaluating proposals set forth in the request for proposals.

## CHAPTER EIGHT

## REQUEST FOR QUOTATION

### 47. *Conditions for use of Request for Quotations*

Public bodies may engage in procurement by means of request for quotations for the purchase of readily available goods or for procurement of works or services for which there is an established market, so long as the estimated value of the contract does not exceed an amount stated in the procurement directive to be issued by the Buréau.

### 48. *Procedure for Request of Quotations*

1. Public bodies shall request quotations form as many candidates as practicable, but from at least three, if possible from among suppliers registered in the suppliers list.
2. In cases where procurements are made using request for quotation, as long as other suppliers, who can supply the same goods, services or works are available, the public body shall not repeatedly invite the same suppliers to submit their quotations. The public body shall ensure that equal opportunity of participation in public procurement is given to all candidates engaged in the business.
3. The request shall contain a clear statement of the requirements of the public body as to quality, quantity, terms and time of delivery of the goods, works, consultancy or other services as well as other special requirements.
4. The public body shall give adequate time to candidates in which to prepare their quotations.

፭. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተዘረዘሩትን ተፈላጊ ሁኔታዎች አሟልቶ እና አነስተኛ ዋጋ ላቀረበ ተወዳዳሪ የግዥ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ
## በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ

### ፵፱. በሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥን ለመፈፀም የሚችሉት የሚከተሉት ሁኔታች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

፩. ለሚገዙት ዕቃዎችና አገልግሎቶች በቂ ዝርዝር ማዘጋጀት በመሥሪያ ቤቱ ደረጃ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም አገልግሎቶችን በሚመለከት ባህሪያቸውን ለይቶ ለማሳየት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ እና የመ/ቤቱን የግዥ ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ለማሟላት የሚያስችል መፍትሔ ለመፈለግ፣

፪. ግዥው የሚካሄደው በገበያ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ዕቃዎችን ለማምረት ወይም የምርምር እና የልማት ወጪዎችን ለመተካት እስካልሆነ ድረስ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የምርምር፣ የሙከራ፣ የጥናት እና የልማት ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ውል መፈፀም ሲፈልግ፣

፫. ጨረታ እንዲወጣ ተደርጎ በሚገዙት ዕቃዎች ፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ፣ የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች ባሕርይ ወይም ተፈጥሮ ግልፅ አለመሆን ምክንያት ዕጩ ተወዳዳሪዎች በጨረታው ያልቀረቡ እንደሆነ ወይም የቀረቡት ተጫራቾች ውድቅ ሲደረጉ እና ይኸም የሆነው መሥሪያ ቤቱ የተሟላ ዝርዝር ማዘጋጀት ባለመቻሉ መሆኑ ሲታመን፣

፬ የሚገዙትን ዕቃዎች፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች፣ የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች ባሕርይ ወይም ተፈጥሮ አስመልክቶ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ጋር ድርድር ማድረግ ሲያስፈልግ፣

5. A purchase order shall be placed with the candidate who meets the requirements stipulated in sub-article (3) of this Article and offered less price.

## CHAPTER NINE
## TWO-STAGE BIDDING

### 49. *Conditions for use of Two-Stage Bidding*

Public bodies may engage in procurement by means of two -stage bidding only where the following conditions are fulfilled:-

1. when it is not feasible for the public body to formulate detailed specifications for the goods or works and in the case of services, to identify their characteristics and, in order to obtain the most satisfactory solution to its procurement needs,
2. when the public body seeks to enter into a contract for the purpose of research, experiment, study or development, except where the contract includes the production of goods in quantities sufficient to establish their commercial viability or to recover the research and development expenses,
3. where bid proceedings are initiated but no bids are submitted as a result of the nature or character of the object of procurement not being clearly described or where all bids are rejected due to failure on the part of the public body concerned to draw up a clear and complete specification,
4. Because of the technical character of the required goods or works, or because of the nature of the consultancy or other services it is necessary for the public body to negotiate with the suppliers.

## ፶ የሁለት ደረጃ ጨረታ አፈፃፀም ሥርዓት

፩. ጨረታው የሚከናወነው በሁለት ደረጃ የጨረታ ዘዴ ሲሆን፣ በመጀመሪያው ዙር ዕጩ ተወዳዳሪዎች ዋጋን ያልጨመረ የመወዳደሪያ ሀሳብ እንዲያቀርቡ በግልፅ ጨረታ ጥሪ ይደረጋል። የጨረታው ሰነድ ከቴክኒክ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መግለጫዎች፣ ጥራት ወይም የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን ሌሎች ባህርያት እንዲሁም የአቅርቦቱን ውል ቃሎችና ሁኔታዎች ሊይዝ የሚገባ ሲሆን፣ አግባብነት እስካለው ድረስ የዕጩ ተወዳዳሪዎችን የሙያ እና የቴክኒክ ችሎታ እንዲገልፁ የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል።

፪ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በመጀመሪያው ዙር የቀረቡትን የመወዳደሪያ 'ሐሳቦች ከግዥ ፍላጎቱ አንፃር በመገምገም ተቀባይነት ያለው የመወዳደሪያ ሐሳብ ያቀረቡ ተጫራቾችን ይለያል። በዚህን ወቅት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ጋር ስላቀረቡት የመወዳደሪያ ሐሳብ የተወዳዳሪዎችን የጨረታ መረጃ እና የባለቤትነት መብት ጠብቆ ውይይት ሊያደርግ ይችላል።

፫. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በመጀመሪያው ዙር የቀረቡትን የመወዳደሪያ ሐሳቦች ከግዥ ፍላጎቱ አንፃር በመገምገም ፍላጎቱን በተሻለ ሊያሟላ የሚችል አንድ ወጥ የሆነ ዝርዝር ያዘጋጃል። የተዘጋጀውን ዝርዝር በመጀመሪያው ዙር ተቀባይነት ያለውን የመወዳደሪያ ሐሳብ ላቀረቡ ተጫራቾች በማሳወቅ ተጫራቾች ዋጋን ጨምሮ በተሻሻለው ዝርዝር መሰረት የመጫረቻ ሐሳባቸውን እና የጨረታ ማስከበሪያ እንዲያቀርቡ ይጋብዛል።

፬. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፫ ላይ በተገለፀው መሠረት መ/ቤቱ አዲስ ዝርዝር ሲያዘጋጅ በመጀመሪያው የጨረታ ሰነድ ውስጥ ከተቀመጡት ማናቸውም የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ የቴክኒክ ወይም የጥራት ባህርያት እና ሰነዶቹን ለመገምገም እና ለማወዳደር እንዲሁም አሸናፊውን ለመምረጥ ከተቀመጡት መስፈርቶች ውስጥ ማናቸውንም ለመሠረዝ ወይም ለማሻሻል ወይም ከዚህ አዋጅ ጋር የሚስማሙ አዳዲስ ባህርያትንና መስፈርቶችን መጨመር ይችላል። እንደዚህ ያሉት ማናቸውም

### 50. *Procedure for Two-Stage Bidding*

1. The solicitation documents shall call upon suppliers to submit, in the first stage of the two-stage bidding proceedings, initial tenders containing their proposals without a tender price. The solicitation documents may solicit proposal relating to the technical, quality or other characteristics of the goods, works or services as well as to contractual terms and services, and conditions of supply, and where relevant the professional and technical competence and qualifications of the suppliers.
2. The public body shall identify responsive bids by evaluation the proposals submitted by the bidders at the first stage of the bid proceeding against it requirements. The public body may without prejudice to their intellectual property rights at this stage hold discussion with the candidates on the content of their proposals.
3. The public body shall draw up a specification which is more appropriate to its requirements on ether basis of the evaluation against the requirements of the proposals submitted to it at the first stage of the bid proceeding. It shall then proceed to communicate the revised specification to the candidates who submitted acceptable bids at the first stage and invite such candidates to submit proposals on the basis of the revised list of auction.
4. In formulating the revised specification in accordance with sub article (3) of this Article, the public body may delete or modify any, aspect, originally set forth in the solicitation documents of the technical or quality characteristics of the goods, works or services to be procured and any criterion originally set forth in those documents for evaluating and comparing bids and for ascertaining the successful bids and may add new

ሥረዛዎች ማሻሻያዎች ወይም ጭማሪዎች የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሳብ እንዲቀርብ በሚተላለፍ ጥሪ ለተጫራቾች መገለፅ አለባቸው።

፭. በተሻሻለው ዝርዝር መሰረት በሁለተኛው ዙር ጨረታ መሳተፍ ያልፈለጉ ተጫራቾች ራሳቸውን ከውድድሩ ማግለል ይችላሉ።

፮. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በሁለተኛው ዙር የቀረቡ የመጫረቻ ሠነዶችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፬ በተደነገገው መሠረት በመገምገም አሸናፊውን ይለያል።

፯. ጨረታውን ያወጣው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በጨረታው ግምገማ ከፍተኛ ውጤት ካገኘው አቅራቢ ጋር ከዋጋ በስተቀር በሌሎች ጉዳዮች ላይ ድርድር ሊያደርግ ይችላል።

## ምዕራፍ አሥር
## በዓለም ዐቀፍ ውድድር የሚፈፀም ግዥ

### ፶፩. ዓለም ዐቀፍ ግዥ

፩. ዓለም ዐቀፍ ግልፅ የጨረታ ዘዴ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የውጭ ኩባንያዎች በጨረታው ተሳታፊ እንዲሆኑ ካልተደረገ በአገር ውስጥ ግልፅ ጨረታ ውጤታማ የሆነ ውድድር ሊኖር እንደማይችል የታመነበት ወይም ግዥው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ ሲሆን ነው።

፪. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እንደተመለከተው ግዥው የቢሮ ኃላፊ በሚያወጣው መመሪያ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ ቢሆንም ምርቱ ወይንም አገልግሎቱ በአገር ውስጥ ብቻ የሚገኝ መሆኑ ከተረጋገጠ ግዥው በአገር ውስጥ ግልፅ ጨረታ ሊካሄድ ይችላል።

፫. ዓለም ዐቀፍ ግዥ በዚህ አዋጅ ምዕራፍ አራት የተጠቀሱትን እና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሥርዓቶች መከተል አለበት።

ሀ/ የጨረታ ማስታወቂያ እና የጨረታ ሰነዶች የዓለም ዐቀፍ ንግድ መገልገያ በሆነው በእንግሊዝኛ ቋንቋ መዘጋጀት አለባቸው።

ለ/ የጨረታ ማስታወቂያው በተዘጋጀበት በእንግሊዝኛ ቋንቋ በሚታተም፣ በቂ ሥርጭት

characteristics or criteria that conform with this proclamation. Any such deletion, modification or addition shall be communicated to suppliers in the invitation to submit final bids.

5. A supplier not wishing to participate in the second stage of tendering in accordance with the reformulated specification may withdraw form the proceeding.
6. The public body shall evaluate the bids submitted at the second stage to ascertain the successful bidder pursuant to the provisions of Article 34 of this proclamation.
7. The public body may engage in negotiation with the first ranking bidder concerning any aspect of its bid, except price.

## CHAPTER TEN
## INTERNATIONAL COMPETATIVE BIDDING

### 51. *Open International bidding*

1. Open International bidding shall be used whenever in national open bidding an effective competition can not be obtained unless foreign firms are invited to bid or for procurements above a threshold level for national bidding to be determined by a directive to be issued by the Bureau .
2. Procurement may be effected by means of national competitive biding not withstanding that the cost of the procurement exceeds the threshold established in the directive for national bidding if it is ascertained that the required object of procurement is available only locally.
3. open international bidding shall respect the provisions of Chapter four of this proclamation as well as the following procedures :-
   a) the invitation to bid and the bid documents shall be in the English language ;
   b) the invitation to bid shall be advertised in a new paper published in English language

ባለው እና ዓለም ዐቀፍ ውድድርን በሚጋብዝ ጋዜጣ እንዲሁም በመመሪያው ላይ በሚገለፀው መሰረት በቢሮዉ ድረ-ገፅ ላይ እንዲወጣ መደረግ አለበት፡፡

ሐ/ የመጫረቻ ሰነድ የማቅረቢያ ጊዜው የጨረታው ማስታወቂያ ለዕጩ ተወዳሪዎች እንዲደርስ ለማድረግ እና ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳባቸውን አዘጋጅተው ለማቅረብ የሚያስፈልጋቸውን በቂ ጊዜ የሚፈቅድ መሆን ያለበት ሲሆን፣ ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ ከሚወሰነው ጊዜ ሊያንስ አይችልም፡፡

መ/ የዕቃና የአገልግሎት ዝርዝር ከአገር ውስጥ ደረጃዎች ጋር የሚጣጣም ሆኖ እስከተቻለ ድረስ በዓለም ዐቀፍ ደረጃዎች ወይም በዓለም ዐቀፍ ንግድ በስፋት የሚሠራበትን ደረጃ መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

ሠ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ዋጋቸውን እንዲሁም የሚያቀርቡትን ማናቸውንም የዋስትና ሰነድ በኢትዮጵያ ብር ወይም በጨረታ ሰነዱ በተመለከተው እና በዓለም ዐቀፍ ንግድ በስፋት በሚሠራበት የገንዘብ ዓይነት እንዲያቀርቡ መፈቀድ አለበት፡፡

ረ/ አጠቃላይ እና ልዩ የውል ቃሎችና ሁኔታዎች በዓለም ዐቀፍ ንግድ የሚሠራባቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

፬. ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ የሚቀመጠው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ለየግዥ ዘዴው የተቀመጡ ሁኔታዎች ሲሟሉ እና የውጪ ኩባንያዎች እንዲሳተፉ ካልተደረገ ውጤታማ የሆነ ውድድር ሊኖር እንደማይችል ሲታመንበት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በውስን ጨረታ፣ በመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ ፣ በዋጋ ማቅረቢያ ወይም ከአንድ አቅራቢ በሚፈፀም ግዥ ዘዴ በመጠቀም ግዢውን በዓለም ዐቀፍ ውድድር መፈፀም ይችላል፡፡

which has world wide circulation and attracts foreign competition as well as on the Bureau' s website in the manner prescribed in the directive;

c) the time allowed for submission of bids shall be sufficient for the invitation to reach candidates and for enabling them to prepare and submit bids . In any case it shall not be less than the time prescribed by the directive to be issued by the Bureau ,

d) technical specifications of the goods ,works and services shall be compatible with national requirements, and conform as far as possible with international standards or standards widely used in international trade;

e) candidates shall be permitted to express their bids , as well as any security documents to be presented by them in Ethiopian birr ,or in a currency widely used in international trade and stated in the bidding document ;

f) General and special conditions of contracts shall be of a kind generally used in international trade.

4. without prejudice to the thresholds be established in the directive to be issue by the Bureau and provided that conditions for using other methods of procurements than open bidding are satisfied , public bodies may conduct procurement through international competitive bidding by means be restricted tendering ,request for proposals ,request for quotation or direct procurement where it is ascertained that it is impossible to carry out successful competition with out the participation foreign companies and without the fulfillments of requirements.

## ምዕራፍ አስራ አንድ

## ልዩ ግዥ

**፶፪. ከፍተኛ ግዥዎች**

፩ ከተማዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ከፍተኛ ግዥዎች፣ ከአንድ በላይ በሆኑ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚፈለጉ አቅርቦቶችን ግዥ እንዲሁም የሚወገዱ ንብረቶችን ሽያጭ የሚፈፅም አካል የአስተደደሩ ካቢኔ በሚያወጣው ደንብ ይቋቋማል::

፪ ቢሮዉ ከተማዊ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆኑ ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተደነገገው መሠረት በሚቋቋመው አካል የሚፈፀሙ ግዥዎችን ዓይነት ይወስናል::

**፶፫. የማዕቀፍ ስምምነት አፈፃፀም**

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ላላቸው ተመሳሳይ የግዥ ፍላጎት ወይም አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ ለሚኖረው የግዥ ፍላጎት ግዥን በማዕቀፍ ስምምነት መፈፀም ይቻላል::

፪/ ከአንድ በላይ በሆኑ መ/ቤቶች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለሚከናወኑ ተመሳሳይ አቅርቦቶች የማዕቀፍ ስምምነት በሚከተለው ሁኔታ ይፈፀማል::

ሀ/ ቢሮዉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚኖራቸውን ተመሳሳይ ፍላጎት በማጥናት የዕቃና አገልግሎቶች ዝርዝር ያወጣል:: በየጊዜውም ዝርዝሩን ያዳብራል::

ለ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ፪(ሀ) በተመለከተው ዝርዝር ውስጥ ለተካተቱት ዕቃና አገልግሎቶች የሚኖራቸውን የፍላጎት ትንበያ አዘጋጅተው ግዥውን እንዲያከናውን ሥልጣን ለተሰጠው አካል ያሳውቃሉ::

## CHAPTER ELEVEN

## SPECIAL POCURENEMENT

**52. *Large value procurement***

1) There shall be established a central body, which shall be in charge of the execution of large value procurements having City wide significances procurements of supplies for which a demand is shown by more than one public body and sale of public property to be disposed off , by a regulation to be issued by the City Government Cabinet .

2) The Bureau shall identify and update the types of procurements to be executed on account of their national significance by the central body which shall be established pursuant to sub article(1) of this Article .

**53. *Procedure of framework contract***

1) Frame work contracts may be used to fulfill similar procurement requirements of various public bodies or recurrent procurement requirements of public body.

2) The following procedure of framework contract shall be followed to meet similar procurement a requirement of public bodies within a given time frame:

a) the Bureau shall undertake a survey of the similar requirements of public bodies, issue a list of goods and services constituting such requirements and update the list regularly;

b) public bodies shall prepare a forecast of their requirements of goods and services falling under the list mentioned in sub article (2)(a) of this article and communicate the same to the body authorized to conduct large procurements.

ሐ/ በአንቀጽ ፶፪(፩) መሠረት የሚቋቋመው አካል በዚህ አዋጅ በተመለከተው እና የቢሮዉ ሃላፊ በሚያወጣው መመሪያ ላይ በሚገለፀው ዝርዝር መሰረት የማዕቀፍ ስምምነት ይፈፅማል ፣ያስተዳድራል፡፡

መ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተፈረመውን የማዕቀፍ ስምምነት መሠረት በማድረግ ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በተፈለገ ጊዜ የግዥ ትዕዛዝ በማስተላለፍ ግዥያቸውን ይፈፅማሉ፡፡

ሠ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው የግዢ ትዕዛዝ የሚያስተላልፉት የማዕቀፍ ስምምነቱ ከተፈፀመበት ዋጋ፣ የክፍያ እና ሌሎች የአፈፃፀም ሁኔታዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ይሆናል፡፡

በግዥ ትዕዛዝ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፴፩ በተመለከተው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ከማዕቀፉ ስምምነቱ የነጠላ ዋጋ ወይም መሰረታዊ በሆኑ ሌሎች የስምምነቱ የውል ሁኔታዎች ላይ ለውጥ ማድረግ አይፈቀድም፡፡ ሆኖም በማዕቀፍ ስምምነቱ ያልተካተቱ እና በማዕቀፍ ስምምነቱ ላይ መሰረታዊ ለውጥ የማያስከትሉ ጉዳዮች የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና የማዕቀፍ ስምምነቱ አቅራቢ በሚያደርጉት ስምምነት ይወሰናሉ፡፡

፬/ የማዕቀፍ ስምምነት የሚፈፀመው በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ ሆኖ፣እስከ ሦስት ዓመታት ድረስ ፀንቶ ሊቆይ ይችላል፡፡

፭/ አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በተደጋጋሚ ለሚኖረው የግዥ ፍላጐት ግዥን በማዕቀፍ ስምምነት ሊፈፅም የሚችለው ቢሮዉ በሚያወጣ መመሪያ የተመለከተውን የዕቃ ወይም የአገልግሎት ዋጋ የሚወስንበትን ግልፅ መስፈርት መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

c) the body to be estaolished in accordance with Article 52(1) of this proclamation shall conclude and administer frame work contracts in the manner prescribed herein and the directive to be issued by the head of Bureau :

d) public bodies shall on the basis of the framework contract signed by the central body of procurement conclude the procurement by making order with the suppliers of goods and service that they require ;

e) the order that public bodies place with the suppliers for goods and services of their requirements under the framework contract shall be conformed to the terms of the framework contract regarded price ,terms of payment and other matters related to the execution of procurement .

3) Except in cases provided for in Article 31 of this proclamation, public bodies shall not be allowed to vary unit price and such other fundamental terms of the frame work contract when placing order for goods and service, However, the public body and the supplier may agree on terms that have not been dealt with in the frame work contract or that do not materially affect the frame work contract.

4) The frame work contract shall be awarded through open bidding procedure and may remain valid for three years.

5) In procuring goods and services under a frame work contract to fulfill their recurrent requirements, public bodies shall have to adhere the criterion of fixing price of goods and services to be determined in the directive to be issued by the Bureau.

## ምዕራፍ አስራ ሁለት

## የመንግስት ንብረት አስተዳደር

**፶፬. አጠቃላይ**

ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የመንግስትን ንብረት በአግባቡ የመያዝ እና የመጠቀም፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የማስወገድ ተግባር መከናወኑን ማረጋገጥ አለበት።

**፶፭. ንብረትን ስለመያዝ**

፩. ማናቸውም የመንግስት ንብረት በባለቤትነት የመያዝ ብቸኛ ዓላማ የፀደቁትን የመስሪያ ቤቱን ፕሮግራሞች ለማስፈፀም እና አገልግሎቱን በማፋጠን ውጤታማና ብቁ ለማድረግ መሆን አለበት።

፪. ቢሮዉ በማናቸውም የአስተዳደሩ መስሪያ ቤት ሥር ያልሆኑትን የከተማ አስተዳደሩን ንብረቶች በመንግስት ንብረትነት ይይዛል፣ ያስተዳድራል፣ ተገቢ ሆኖ ሲያገኝም እንዲወገዱ ያደርጋል ።

**፶፮. አጠቃቀም እና ጥገና**

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ማናቸውም የመንግስት ንብረት የመስሪያ ቤቱን ኃላፊነት ውጤታማ በሚያደርግ መልኩ አገልግሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ አለበት።

፪. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገቢ የጥገና እና የእንክብካቤ ሥርዓት መዘርጋት አለበት።

**፶፯. የመንግስት ንብረት አስተዳደር**

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የመንግስት ንብረት ለማስተዳደር የሕይወት ዘመን ሥርዓትን ይከተላል።

፪. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የመንግስት ንብረት ከተያዘበት፣ ከአገልግሎት ውጪ እስከሆነበት ቀን ድረስ ንብረቱ አገልግሎት ያቋረጠበትን ጊዜ ፣ የንብረቱን አይነት ፣ ብዛቱን እና ያስከተለውን ወጪ የሚያሳይ ዝርዝር ተመዝግቦ መያዙን ማረጋገጥ አለበት።

## CHAPTER TWELVE

## PUBLIC PROPERTY ADMINISTRATION

**54. *General***

Each public body shall ensure that property at the disposal of public body is properly handled, used and where necessary, disposed of in accordance with the directive to be issued by the Bureau.

**55. *Acquisition***

1) All acquisitions of public property shall be for the sole purpose of facilitating the delivery and maintenance of approved programs as regards service.

2) The Bureau shall account for administer and where necessary, dispose off property of the City Government which are not administered by any other public body.

**56. *Use and maintenance***

1) Heads of public bodies shall ensure that all public property is used as productively as possible in carrying out of the responsibilities of the public bodies.

2) Heads of public bodies shall established a proper maintenance system for all public property to ensure that it will operate as economically and effectively as possible in accordance with the directives to be issued by the Bureau.

**57. *Management of Public property***

1. The Heads of public bodies shall adopt a life time approach to the management of public property.

2. Heads of public bodies shall ensure that items of public property are recorded as to date, description quality and cost from acquisition to the end of their life time.

፫. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የመስሪያ ቤቱን ማናቸውንም ቋሚ ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነት በመጀመሪያ ደረጃ ንብረቱን እንዲገለገሉበት ኃላፊነት ለተሰጣቸው ኃላፊዎች መስጠቱን እና በቋሚ ንብረት መዝገብ የጠባቂዎቹ ዝርዝር እና በእነርሱ ጥበቃ ስር ያሉት ቋሚ ንብረቶች የሚገኙበት ቦታ መስፈሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፬. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የማይውሉ አላቂ ዕቃዎች በመሥሪያ ቤቱ የሚመለከተው የንብረት ሥራ ክፍል በዕቃ ዝርዝር መዝገብ ውስጥ መካተታቸውንና ለጥበቃቸው ኃላፊ መመደቡን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፭. ማናቸውም የመንግስት ንብረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መቆጠር አለበት፡፡

፮. የመንግስትን ንብረት ትክክለኛ ዋጋ ለመወሰን ሳይቻል ሲቀር ግምቱ የቢሮው ሃላፊ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል፡፡

፯. ቢሮው በሚያወጣው ዝርዝር መመሪያ መሰረት የሚፈፀም ሆኖ በመንግስት ቋሚ ንብረት ላይ የእርጅና ቅናሽ ይሰላል፡፡

## ፶፰. መጠበቅና መንከባከብ

ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ እና ሠራተኞች የመንግስትን ንብረት የመጠበቅና የመንከባከብ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## ፶፱. ማስወገድ

፩. ዝርዝር አፈፃፀሙ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች መወገዳቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፪. የተወገደ የመንግስት ንብረት መግለጫና ንብረቱን በማስወገድ የተገኘው ገንዘብ በመንግስት ሒሳብ ሪፖርት ውስጥ መጠቃለል አለበት፡፡

3. Heads of public bodies shall ensure that the custodial responsibility for each fixed asset acquired is assigned primarily to persons using such fixed assets and that names of the custodians, and the locations of the fixed assets under their custody are recorded in the register of fixed assets.

4. Heads of public bodies shall ensure that supplies, not acquired for immediate consumption, shall form part of supply inventories an that custodial responsibility be assigned for such inventories.

5. All inventories of public property shall be physically verified against records at least annually.

6. Where the actual cost of public property is not determinable, its costs shall be estimated in accordance with the directive to be issued by the head of Bureau.

7. Depreciation shall be calculated on fixed assets in accordance with the directive to be issued by the Bureau.

## 58. *Protection and preservation*

The Heads and all employees of public bodies are responsible for the protection and preservation of public property .

## 59. *Disposal*

1. Public bodies shall ensure that fixed assets which are not useful to the organization are disposed off in the manner to be prescribed in the directive to be issued by the Bureau.

2. The description and amount received from all public property disposed off shall be included in the public accounts.

፫. ቢሮዉ በሚወጣ መመሪያ የሚወሰነው እንደ ተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግስትን ንብረት በማስወገድ የተገኘ ገቢ ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

**፷. መሠረዝ**

፩. የመንግስት ንብረት ለሚገኝበት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም ለሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት የማይጠቅምና ዋጋ የማያወጣ መሆኑ ሲረጋገጥ ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይሰረዛል፡፡

፪. የመንግስት ንብረት ሲበላሽ ከጥቅም ውጪ ሲሆን ሲሰረቅ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ምክንያት ሲጎድል ወይም ሲጠፋ ከንብረት መዝገብ ይሰረዛል፡፡

፫. ማናቸውም የመንግስት ንብረት ሲሰረዝ መግለጫውና የንብረቱ የመዝገብ ዋጋ ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በመንግስት ሒሳብ ሪፖርት ውስጥ ተጠቃልሎ መታየት አለበት፡፡

**፷፩. ማስተላለፍ**

ለአንድ መሥሪያ ቤት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ለሌላ የከተማ አስተዳደሩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ወይም ለሌሎች የመንግሥትን ኃላፊነት የማገዝ ተግባር ለሚያከናውኑ አካላት በስጦታ የሚተላለፉበትን ሁኔታ ቢሮዉ በመመሪያ ይወስናል፡፡

## ምዕራፍ አስራ ሦስት

## በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አወጋገድ ሂደት ስለሚቀርብ አቤቱታ

**፷፪. ጠቅላላ**

፩. የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ግዥውን በሚፈፅመው ወይም ንብረቱን በሚያስወግደው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተከናወነው ወይም ሳይከናወን የቀረው ተግባር ይህንን አዋጅ እና የአፈፃፀም መመሪያዎቹን ይጥሳል ብሎ የሚያምን ዕጩ ተወዳዳሪ ለመሥሪያ

3. Without prejudice to the provision of the directive to be issued by the Bureau, concerning the matter, proceeds from the disposal of public property shall be deposited into the account of Finance and Economic Development Bureau.

**60. *Deletion***

1. Where public property is considered to be of no use in the public body or else where, and has no-scrap value, it shall be deleted in accordance with the directive to be issued by the Bureau.
2. Deletion of public property shall be recorded when losses take place from inventory shortages, destruction, theft or any other reason.
3. The description and book value of all public property deleted shall be included in the public accounts in accordance with the directives to be issued by the Head of Bureau.

***61. Transfer***

The head of Bureau shall determined by directive the manner in which property which is not useful to one public body may be transferred gratis to another public body of the City Government or any other body carrying on activities complementing the responsibility of the City Government .

## CAHPTER THRTEEN

## COMPLAINTS THAT MAY BE LODGED WITH REGARD TO PROCEEDINGS OF PUBLIC PROCUREMENT AND PEROPERTY DISPOSAL

**62. *General***

1. Without prejudice to the provisions of this Chapter, a candidate shall be entitled to submit a compliant to the head of the public body or to the Bureau against an act or omission of the public body in regard to a public

ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም በደረጃ ለቢሮው ሊያቀርብ ይችላል::

፪. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተደነገገው መሠረት አቤቱታ ሊቀርብባቸው አይችልም::

ሀ/ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሚከናወን የግዥ ዘዴዎች ምርጫ፣

ለ/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፪ መሠረት ጨረታን፣ የመወዳደሪያ ሀሳብን ወይም የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ ማድረግ፣

ሐ/ የመንግስት መ/ቤቱ ንብረቱን ለማስወገድ በመረጠው የማስወገጃ ዘዴ፣

መ/ በመንግስት ንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም ላይ፣

፫. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በጨረታው አሸናፊ ከሆነው ተወዳዳሪ ጋር የግዥ ውል ከፈረመ በኋላ፣ ሂደቱ ከዚህ ደረጃ እስከሚደርስ ድረስ በመሥሪያ ቤቱ በተከናወኑ ወይም ሳይከናወኑ በቀሩ ተግባራት ምክንያት የሚቀርቡ አቤቱታዎች በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ወይንም በቢሮው ሊታዩ አይችሉም::

፬ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተደነገገው ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው::

ሀ/ ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ ላይ በሚቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ አቤቱታ ባለመቅረቡ ውል የተፈረመ ከሆነ፣

ለ/ አቤቱታ ቀርቦ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ምላሽ የሰጠ እና ቢሮጢ በሚያወጣው መመሪያ ላይ አሸናፊው ከተገለፀ በኃላ ውል ለመፈረም የተቀመጠው ጊዜ ገደብ በመጠናቀቁ ውል የተፈረመ ከሆነ፣

፭. በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ ላይ ስለሚቀርብ አቤቱታ እና ዝርዝር አፈፃፀም ቢሮጢ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

procurement or property disposal proceeding where he believes that such commission violates the Proclamation or the Directives which the head of Bureau will issue.

2. No compliant may be lodged in accordance with sub-Article(1) of this Article in respect of the following matter :-
   a) the selection of procurement method pursuant to this proclamation ;
   b) the rejection of bids proposal or quotations pursuant to Article 22 of this Proclamation;
   c) the selection of method of property disposal ;
   d) the handling and usage of public property.

3. Complaints against an act or omission of a public body pertaining to a proceeding le~ding to an award may not be brought before the head of that public body or the Bureau after the contract has been signed with the successful bidder.

4. The provisions of sub-article (3) of this Article shall apply where the following conditions are satisfied:
   a) where the contract has been signed without a compliant being filed with the public body within the time limit prescribed in the Directive issued by the Bureau;
   b) Where the public body responded to the compliant lodged and a contract is signed because of the expiration of the time limit for the signing of contract after the award without the candidate pursuing its compliant further.

5) The procedure to be followed in resolving complaints brought in regard to public procurement and property disposal shall be determined in accordance with the directive to be issued by the Bureau

፷፫. <u>ለመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊዎች ስለሚቀርቡ አቤቱታዎች</u>

፩. በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በተከናወነ ወይም ሳይከናወን በቀረ ተግባር ምክንያት የሚቀርብ አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃ መቅረብ ያለበት ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይሆናል፡፡

፪. ዕጩ ተወዳዳሪው አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችለው ለአቤቱታው መሠረት የሆነውን ውሣኔ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ በ፭ የሥራ ቀን ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡

፫. አቤቱታው በሁለቱ ወገኖች መካከል በሚደረግ ስምምነት ካልተፈታ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የግዥውን ወይም የንብረት ማስወገዱን ሒደት ማገድ እና አቤቱታው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በአሥር የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ፣ ውሣኔው የተሰጠበትን ምክንያት ወይም አቤቱታው ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ የሚወሰደውን የማስተካከያ እርምጃ በመጥቀስ የፅሑፍ ውሣኔ መስጠት አለበት፡፡

፬. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ካልሰጠ ወይም ተወዳዳሪው በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ውሣኔ ያልረካ እንደሆነ የመሥሪያ ቤቱ ውሣኔ ለአቤቱታ አቅራቢው መገለፅ ከነበረበት የመጨረሻ ቀን ወይም ውሳኔ የሰጠ ከሆነም ውሳኔው ከተገለፀለት ቀን አንስቶ በሚቆጠር ፭ የሥራ ቀን ጊዜ ውስጥ ለቢሮው ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፷፬. <u>ለቢሮው የሚቀርቡ አቤቱታዎች</u>

፩. ቢሮው አቤቱታ ሲቀርብለት ወዲያውኑ አግባብ ላለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት አቤቱታ የቀረበ መሆኑን የሚገልፅ ማስታወቂያ በፅሕፈት ቤት በኩል ይልካል፡፡ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱም ቢሮው በጉዳዩ ላይ ውሣኔ እስከሚሰጥ ድረስ ማናቸውንም ቀጣይ እንቅስቃሴ ወዲያውኑ ማቆም አለበት፡፡

63 ***Review of complaints by the head of the public body***

1) A compliant against an act or omission by the public body shall in the first instance, be submitted to the head of the public bodies.
2) A candidate shall have to submit the compliant within five working days from the date he knew or should have known the circumstance giving rise to the compliant.
3) Unless the compliant is resolved by mutual agreement ,the head of the public body shall suspend the procurement or property disposal proceeding and shall ,within 10 days after submission of the compliant ,issue a written decision stating the reasons, and if the compliant is upheld, indicating the corrective measures to be taken..
4) If the head of the public body does not issue a decision with in the time stated in the sub Article (3) of this Article, or if the candidate is entitled to submit a compliant to the Bureau within five working days from the date on which the decision has been communicated to the candidate by the public body.

64. ***Review by the Bureau***

1) Upon receipt of a compliant, the Bureau shall promptly give written notice of the compliant to the public body concerned. Such action automatically suspends further action by the public body until the Bureau has settled the matter.

፪. ቢሮው የዕጩ ተወዳዳሪውን አቤቱታ ውድቅ ካላደረገው በስተቀር፣
   ሀ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሕጉን ያልጠበቀ ተግባር እንዳያከናውን እና ውሣኔ እንዳይሰጥ ሊያግድ፣
   ለ/ አሸናፊውን ተጫራች ከመምረጥ ወይም ውል ከመፈረም ጋር ከተያያዙ ውሣኔዎች በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሥራውን እንዲያከናውን፣
   ሐ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከሕግ ውጪ ያከናወነው ተግባር ወይም የሰጠው ውሣኔ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን፣
   ውሣኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡
፫. ቢሮው በአቤቱታ ላይ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ስለአቤቱታው ማወቅ ለሚገባቸው አካላት ማሳወቅ፣ ከእነዚህ አካላት የቀረበ መረጃ እና መከራከሪያ ሐሳብ ካለ ይህንኑ መመርመር አለበት፡፡

፬. ቢሮው አቤቱታው ከቀረበለት ቀን አንስቶ በ፲፭ የስራ ቀናት ውስጥ ለውሣኔው መሠረት የሆኑትን ምክንያቶች እና የተወሰዱትን የመፍትሔ እርምጃ-ዎች በመጥቀስ ውሣኔ መስጠት አለበት፡፡

## ፷፭. ከመንግስት መስሪያ ቤቶች ለቢሮው ስለሚቀርብ አቤቱታ

፩. በመንግስሥት ግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አወጋገድ ሒደት የመንግስት መ/ቤት ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ከአቅራቢዎች ወይም ከሚወገድ ንብረት ገዥዎች ሕገ ወጥ የሆነ ወይንም ሕጋዊ የሆነ ጥቅሜን የሚጎዳ ድርጊት ተፈፅሞብኛ ብሎ ሲያምን በጨረታ ሰነዱ ወይንም በኮንትራት ስምምነቱ መሰረት የሚወስዳቸው እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ጉዳዩን ለቢሮው በፅሑፍ ያቀርባል፡፡
፪. ቢሮው ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አቤቱታ ሲቀርብለት አቤቱታ የቀረበ መሆኑን እና የአቤቱታውን ፍሬ ሐሳብ የሚገልፅ የፅሑፍ ማስታወቂያ አቤቱታ ለቀረበበት ዕጩ ተወዳዳሪ ወይንም አቅራቢ ወይንም የሚወገድ የመንግስት ንብረት ገዥ ይልካል፡፡

2) The Bureau, unless it dismisses the compliant, may:
   a. prohibit the public body from acting and deciding unlawfully ;
   b. order the public body to proceed in a manner conforming to this proclamation other than a decision to award or conclude a contract ;
   c. annul in whole or in part, an unlawful act or decision by the public body.
3) The Bureau shall, before taking any decision regarding a compliant, notify relevant bodies of the compliant and shall take into account information and argument received from such bodies and from the public body.
4) The Bureau shall issue its decision within 15 working days of receiving the compliant, stating the reasons for its decision and remedies granted, if any.

## 65. *Complaint presented by the Public Bodies to the Bureau*

1) where a public body believes that an unlawful act or an act prejudice to its legitimate interest has been committed by candidates, suppliers or by buyers of disposed property, it shall with out prejudice to the measures it is entitled to take against such persons in accordance with the bidding document or the contract, notify the matter in writing to the Bureau.
2) Upon receipt of the compliant the Bureau shall send a written notice of the compliant and the content of such compliant to the candidate, the supplier or the buyer of disposed property against whom the compliant has been lodged.

፫. ቢሮው አቤቱታውን ለመመርመር እና ውሳኔ ለመስጠት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ጠርቶ ማነጋገር ወይንም መረጃ መጠየቅ እና ማግኘት እንዲሁም ከማንኛውም አካል የሙያ ድጋፍ መጠየቅ እና ማግኘት ይችላል፡፡

፬. ቢሮው የቀረበለትን አቤቱታ በተገቢው በመመርመር አቤቱታው በቀረበለት በ ፲፭ የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፭ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፬ መሰረት ቢሮው የሚሰጠው ውሳኔ ከሚከተሉት አንዱን ሊሆን ይችላል፡፡

ሀ. ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘውን ዕጩ ተወዳዳሪ ወይንም አቅራቢ ወይንም የሚወገድ ንብረት ገዥ በማንኛውም የመንግስት ግዥ እና ንብረት አወጋገድ ሒደት ለተወሰነ ወይንም ላልተወሰነ ጊዜ እንዳይሳተፍ የማገድ

ለ. የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት

ሐ. የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ የማድረግ

፮ ቢሮው ከመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች የሚመረምርበትን እና ውሳኔ የሚሰጥበትን አሰራር የሚያሳይ መመሪያ በቢሮው ሃላፊ ፀድቆ ስራ ላይ እንዲዉል ያደርጋል፡፡

## ምዕራፍ አስራ አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፷፮. ጥፋቶችና ቅጣቶች

ይህን አዋጅ በመጣስ ጥፋት ቢፈፀም በቻርተሩና በሌሎች አግባብነት ባላቸዉ ህጎች የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የግዢና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፱/፪ ሺህ ፩ አንቀፅ ፸፯ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3) Where the Bureau finds it appropriate to the resolution of the compliant it may require persons concerned with the matter to appear in person and give evidence or seek professional assistance from any appropriate body.

4) The Bureau shall review and give decision on the compliant within 15 working days of receipt of such compliant.

5) The decision to be rendered by the Bureau in accordance with sub-article (4) of this Article may be one of the following :-

   a. Suspending the candidate or supplier or purchaser of diposed public property, who has committed fault, from participating in any process of public procurement and disposal of public property for defined or undefined period of time;
   b. Giving written notice;
   c. Rejecting the complaint submitted.

6) The head of Bureau shall cause a directive, providing for the procedure the Bureau follows in reviewing and deciding complaints submitted to it in accordance with this Article, issued and implemented.

## PART FOURTEEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 66 *Offences and Punishments*

Without prejudice to the provisions of the Charter and other relevant laws, when offences are committed by violating this Proclamation, Article 77 of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Government Procurement and Property Administration Proclamation No. 649/2009, shall apply.

**፷፯. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ እንደአስፈላጊነቱ ደንብ ሊያወጣ ይችላል::

፪. ቢሮዉ የዚህን አዋጅ ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ እና የአዋጁን ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ መመሪያ-ዎችን ሊያወጣ ይችላል::

፫. ቢሮዉ ይህንን አዋጅ እና የቢሮው ሃላፊ የሚያወጣውን የአፈፃፀም መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ማኑዋል፣ መደበኛ የጨረታ ሰነድ፣ የግዥ አፈፃፀምን እና የንብረት አስተዳደርን የሚመሩ ልዩ ልዩ ቅፆችን ያወጣል::

**፷፰. <u>የተሻሩና ተፈፃሚ የማይሆኑ ሕጐች</u>**

፩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዥ ሥርዓትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፳፰/፲፱፻፺፱ ዓ.ም. ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል::

፪. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

**፷፱. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፴ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል::

*አዲስ አበባ*
ጥቅምት ፴ ቀን ፪ሺህ፪ ዓ.ም

*ኩማ ደመቅሳ*
የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

**67. *Power to issue Regulation and Directives***

1) The Addis Ababa City Government Cabinet may issue regulation for the implementation of this Proclamation

2) The Bureau may issue directives enabling the realization of the objectives and implementing the provisions of this proclamation.

3) The head of Bureau shall issue procurement and property administration manuals, standard bid documents, and forms that are necessary for the implementation of public procurement and property administration.

**68. *Repealed and Non-Applicable Laws***

1) The Addis Ababa City Government Procurement and Property Proclamation No. 28/1999 is hereby repealed and replaced by this proclamation.

2) Any Proclamation, regulation, directive or practices inconsistent with this proclamation shall have no effect with respect to matters provided for in this proclamation.

**69. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force as of 9th day of November 2009.

**Addis Ababa**
**Done at this 9th day of November /2009**

**Kuma Demeksa**
**Mayor of Addis Ababa City**